# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## በቱሪዝም ሚኒስቴር የቱሪዝም መዳረሻ ልማትና አገልግሎት አሰጣጥ አፈጻጸምን በተመለከተ የተካሄደ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

ሚያዚያ 2017 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ማውጫ


ማውጫ ..... i

የዋና ዋና ግኝቶች ማጠቃለያ (Executive Summery) ..... I

ክፍል አንድ ..... 1

መግቢያ ..... 1

የሚኒስቴር መ/ቤቱ ታሪካዊ ዳራ ..... 1

የሚኒስቴር መ/ቤቱ ራዕይ እና ተልዕኮ ..... 2

ራዕይ ..... 2

ተልእኮ ..... 2

የቱሪዝም ሚኒስቴር ሥልጣንና ተግባራት ..... 2

የቱሪዝም ሚኒስቴር ድርጅታዊ አወቃቀር ..... 4

የቱሪዝም መዳረሻና የመሰረተ ልማት የስራ ክፍል የስራ ፍሰት መግለጫ /Process Description/ ..... 4

የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሰው ኃይል ..... 5

የሚኒስቴር መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ ..... 5

የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ ..... 6

የኦዲቱ ወሰን ..... 6

የኦዲቱ ዘዴ ..... 6

ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ ..... 7

የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ..... 7

የኦዲት መመዘኛ መስፈርት ..... 7

ክፍል ሁለት ..... 8

የኦዲት ግኝቶች ..... 8

የቱሪስት መዳረሻ ሥፍራዎች መሰረተ ልማት እንዲሟላ የአሰራር ማዕቀፍ ዝግጅትን በተመለከተ ..... 8

የቱሪዝም ኢንቨስትመንት ለማበረታታት ጥናት መከናወኑን በተመለከተ ..... 9

የቱሪስት መስህብና መዳረሻ በታዎች ማሟላት ያለባቸውን የመሰረተ ልማት ስታንዳርድ ስለመዘጋጀቱ በተመለከተ ..... 12

የብሔራዊ ፓርኮች የመሰረተ ልማት ስታንዳርድ ዝግጅትን በተመለከተ ..... 13

የቱሪስት መዳረሻ የመሰረተ ልማት የተሟላላቸው መሆኑንና የክፍተት ጥናትን መከናወኑን በተመለከተ ..... 14

የቱሪስት መዳረሻ ፕሮጀክቶች አፈፃፀምን በተመለከተ ..... 19

የፓርክ አስተዳደር ዕቅድ /General Management Plan/ ትግበራን በተመለከተ ..... 24

በብሔራዊ ፓርኮች የጤና ተቋማት ስለመቋቋማቸው በተመለከተ ..... 25

የቱሪስት መዳረሻ የውስጥ ለውስጥ መንገድ ዝርጋታን በተመለከተ ..... 26

የቱሪስት አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች ደረጃ ምደባን በተመለከተ ........ 29
የደረጃ ምደባ የተደረገላቸው ሆቴሎች ላይ የሚከናወን ክትትልን በተመለከተ ........ 30
የሆቴሎች የመጀመሪያ እና የዳግም ደረጃ ምደባን በተመለከተ ........ 35
ዘመናዊ የቱሪዝም መረጃ ስርዓትን በተመለከተ ........ 37
በመዳረሻ ስፍራዎች የሚያስፈልጉ ፋሲሊቲዎች ተለይተው ስለመደራጀታቸው በተመለከተ ........ 38
በመዳረሻዎች የቱሪስት እርካታ ደረጃ መመዘኛ ሥርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ ........ 40
ዘመናዊ የቱሪዝም መዳረሻ ስርዓትን በተመለከተ ........ 41
ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ስትራቴጂካዊ ግንኙነትና ቅንጅታዊ አሠራር መመስረቱን በተመለከተ፡ ........ 42
ከክልልና ከፌዴራል የቱሪዝም አካላት ጋር በጋራ ለመስራት የሚያስችል ማዕቀፍ ስለመዘጋጀቱ ........ 43
የቱሪዝም ቦርድ ስለመቋቋሙ በተመለከተ ........ 44
ክፍል ሦስት ........ 46
መደምደሚያ/Conclusion ........ 46
ክፍል አራት ........ 49
የማሻሻያ ሀሳብ /Recommendation/ ........ 49
አባሪ 1 የሚኒስቴሩ ድርጅታዊ መዋቅር ........ i
አባሪ 2፡ ኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ........ ii
አባሪ ሦስት፡ በኦዲት ቡድኑ በዕቅድ ተይዘው የታዮ የመስክ ስፍራዎች/ መ/ቤቶች ........ iv

# የዋና ዋና ግኝቶች ማጠቃለያ

## (Executive Summery)


የክዋኔ ኦዲቱ የተከናወነው ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ስልጣን መሰረት በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ቱሪዝም ሚኒስቴር መ/ቤት የቱሪስት መዳረሻ ልማት እና አገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማነትን ለመገምገም የተከናወነ ሲሆን፤ ኦዲቱ የሸፈነው ከ2014 እስከ 2017 በጀት ዓመት ሁለተኛ ሩብ ዓመት ድረስ ያሉትን ጊዜያት ነው። የኦዲቱ ዓላማ የቱሪዝም ሚኒሰቴር የቱሪዝም መዳረሻ ልማትና አገልግሎት አሰጣጥ ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ እየተከናወነ ስለመሆኑ በመገምገም በስራው ዙሪያ የአሰራር ክፍተቶች ካሉ በመለየት ችግሮቹን ለመቅረፍ ወይንም ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሀሳቦችን ማቅረብ እንዲሁም ተጠያቂነትን ማስፈን ነው። በዚህም መሰረት በኦዲቱ ወቅት በመ/ቤቱ የሚከተሉት ዋና ዋና የአሰራር ክፍተቶች ተገኝተዋል፦

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በቱሪስት መዳረሻ ቦታዎች መሟላት ያለበትን መሰረተ ልማቶችና ፋሲሊቲዎች አነስተኛ መስፈርት/ ስታንደርድ አልተዘጋጁም፣ የፓርክ አስተዳደር ፕላን (Park Management Plan) ያልተዘጋጀላቸው ብሔራዊ ፓርኮች አሉ የተዘጋጀላቸውም በፕላኑ መሰረት ወደ ተግባራ አልገቡም፣
- ብሔራዊ ፓርኮች ሲቋቋሙ ከመሰረተ ልማት አኳያ ማሟላት ያለባቸውን መስፈርት የሚገልጽ ስታንዳርድ አልተዘጋጀም፤
- በብሔራዊ ፓርኮችም ሆነ በሌሎች የቱሪስት መዳረሻ ሥፍራዎች መሟላት የሚገባቸው መሰረተ ልማቶች እንደ ውስጥ ለውስጥ መንገድ፣ የተለያዩ አገልግሎት መስጫ (መብራት፣ ውሃ፣ የቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎቶች ሎጅ፣ ምግብ ቤቶች፣ ሱቆች፣ የመጸዳጃ ቤቶች፣ የመሳሰሉት) ተቋማትና አቅርቦቶች አልተሟላም: የተበላሹም አሉ፣




**ወደ ሰንቀሌ ብሔራዊ ፓርክ የሚያስገባው መንገድ**

- በቱሪዝም ኢንቨስትመንት ዘርፍ የሚሰጡ ማበረታቻዎች ለታለመላቸው ዓላማ መዋላቸውን ክትትል አይድረግም፣ የተሰጡ ማበረታቻዎችም መረጃቸው ተጠናቅሮ አይያዝም፣
- በሚኒስቴር መ/ቤቱ፣ ተጠሪ በሆኑ ተቋማት እና በሌሎች አካላት በስንቅሌ የቆርኬዎች መጠለያ እየተከናወኑ ያሉ ፕሮጀክቶች እና የመሰረተ ልማት ሥራዎች በተያዘላቸው በጀት እና ጊዜ ደረጃቸውን ጠብቀው እየተከናወኑ አይደለም፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የቱሪስት አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች ከሆቴሎች በስተቀር

ለሌሎቹ (ሬስቶራንት፣ ሎጅ፣ ፔንሲዮን፣ የባህል ምግብ ቤቶች፣ አስጎብኝ ድርጅቶች) በየደረጃቸው ማሟላት የሚገባቸውን ዝርዝር መስፈርት የሚገልጽ መመሪያ አላዘጋጀም፤


- ከቀረጥ ነጻ እቃዎችን አስገብተው አገልግሎት መስጠት የጀመሩ አንዳንድ አዳዲስ ሆቴሎች በተቀመጠው አሰራር መሰረት ሥራ ከጀመሩ በአንድ አመት ውስጥ መመዘንና ደረጃ ሊሰጣቸው ቢገባም አለመከናወኑ፣

- በምዘና መመሪያው አስገዳጅ ተብለው የተቀመጡት መስፈርቶች በተለይ የእሳት አደጋ መከላከያ መስፈርቶች ሳይሟሉ ደረጃ የሚሰጥ መሆኑ፣




- የደረጃ ምደባ ከተከናወነ በኃላ ውጤቱ የሆቴሎች ደረጃ ምደባ መመሪያ ቁ.1/2014 በሚያዘው መሰረት የምደባው ውጤት ለተመዘነው ድርጅትም ሆነ ለህዝቡ ይፋ አለመደረጉና እስከ ሁለት አመት የሚዘገይ መሆኑ፣

- የኮከብ ደረጃ በተሰጣቸው ሆቴሎች ላይ በአንድ ዓመት ጊዜያት ውስጥ መደበኛ በሆነ መልኩ ሁለት ጊዜ የክትትልና ቁጥጥር ስራ ማከናዎን እንደሚገባ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተዘጋጀው የሆቴሎች የደረጃ ምደባ መመሪያ ቁ.1/2014 የሚያዝ ቢሆንም ይህ አሰራር የማይተገበር መሆኑን፤ ክትትል ሲደረግም የተዘጋጀውን ቼክሊስት በከፊል የሚጠቀሙ መሆኑ፤




- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ቱሪዝም ልማት ዘርፍ የሚመለከታቸውን የግል፣ የፌዴራል እና የክልል መንግስት ተቋማትን በማስተባበር የኢትዮጵያ ቱሪዝም ቦርድ አላቋቋመም፣

የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፤ ከላይ ለተመለከቱት ዋና ዋና ግኝቶች መፍትሄ ሊሆኑ የሚችሉ የማሻሻያ ሃሳቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በቱሪስት መዳረሻ ቦታዎች መሟላት ያለበትን መሰረተ ልማቶችና ፋሲሊቲዎች አነስተኛ መስፈርት/ ስታንደርድ ሊያዘጋጅና ከክልችና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ወደ ትግበራ ሊያስገባ ይገባል፡፡

- ለብሔራዊ ፓርክነት ለመመረጥ መሟላት ያለበትን ዝቅተኛ መስፈርትና አስፈላጊ የአገልግሎት መስጫ ተቋማት በግልጽ ተለይተው ሊቀመጡና በዚህ መስፈርት መሰረት ሊቋቋሙ ይገባል፡፡

- በአገሪቱ ተቋቋመው አገልግሎት በመስጠት ላይ ያሉ ብሔራዊ ፓርኮች ውስጥ የፓርክ አስተዳደር ዕቅድ (Park Management Plan) የተዘጋጀላቸው በዕቅዱ መሰረት ወደ ተግባር ሊገቡ እና ሚኒስቴር መ/ቤቱም ተግባራዊነታቸውን ሊቆጣጠር ይገባል። የፓርክ አስተዳደር ዕቅድ (Park Management Plan) ያልተዘጋጀላቸው ብሔራዊ ፓርኮችም ዕቅዱን በማዘጋጀት ወደተግባር ሊገቡ የሚገባና ሚኒስትር መ/ቤቱም ይህ በዕቅድ ተይዞ መተግበሩን በባለቤትነት ሥራውን የሚመራውን ተቋም ሊከታተል ይገባል።

- በብሔራዊ ፓርኮች ሆነ በሌሎች የቱሪስት መዳረሻ ሥፍራዎች መሟላት የሚገባቸው መሰረተ ልማቶች እንደ ውስጥ ለውስጥ መንገድ፣ የተለያዩ አገልግሎት መስጫ (መብራት፣ ውሃ፣ የቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎቶች ሎጅ፣ ምግብ ቤቶች፣ ሱቆች፣ ህክምና መስጫዎች፣ የመጸዳጃ ቤቶች፣ የመሳሰሉት) ተቋማትና አቅርቦቶች ሊሟሉላቸውና ያልተሟሉትንም በጥናት በመለየት የየሚሟሉበት ሁኔታ ሊያመቻች ይገባል። በተለይ በብሔራዊ ፓርኮች ውስጥ ቱሪስቶች መስህቦቹን በመዘዋወር በቀላሉ መጎብኘት እንዲችሉ የውስጥ ለውስጥ መንገዶች ደረጃቸውን የጠበቁ ሊሆኑ እና በየጊዜው እንክብካቤና ጥገና ሊከናወንላቸው የሚገባና ይህ መተግበሩንም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሊያረጋግጥ ይገባል።

- በሚኒስቴር መ/ቤቱ፣ ለእርሱ ተጠሪ በሆኑ ተቋማት እና በሌሎች አካላት የቱሪስት መዳረሻ ቦታዎች እየተከናወኑ ያሉ ፕሮጀክቶች እና የመሰረተ ልማት ሥራዎች በተያዘላቸው በጀት እና ጊዜ ደረጃቸውን ጠብቀው እየተከናወኑ መሆናቸውን ሚኒስቴር መ/ቤቱ የቅርብ ክትትል ሊያደርግና በየጊዜው በመገምገም ግበረ መልስ በመስጠትና ተጠያቂነትን ጭምር በማስፈን እንዲጠናቀቁ በማድረግ ጎብኙዎች ደረጃውን የጠበቀ አገልግሎት እንዲያገኙ ሊያድግና መስህቦቹ ለሚገኙባቸው ህብረተሰብ ክፍሎች የሥራ ዕድል የሚፈጠርበትን ሁኔታ ሊያመቻች ይገባል።

- ሚኒስቴር/መቤቱ የቱሪስት አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች ከሆቴሎች በስተቀር ለሌሎቹ (ሬስቶራንት፣ሎጅ፣ ፔንሲዮን፣ የባህል ምግብ ቤቶች፣ አስጎብኝ ድርጅቶች፣) በየደረጃቸው ማሟላት የሚገባቸውን ዝርዝር መስፈርት ሊያወጣላቸውና በኢትዮጵያ ደረጃዎች አገልግሎት በማቅረብ ደረጃዎቹን ሊያጸድቅና ወደ ትግበራ ሊገባ ይገባል።

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሆቴሎች የደረጃ ምደባ አገልግሎት በአደረጃጀት የታገዘ እና በዕቅድ ላይ የተመሰረተ እንዲሆን በማድረግ በዘመቻ መልክ የሚከናወነውን የምደባ ሥራ ማስቀረት ይጠበቅበታል።

- ተገንብተው ወደ አገልገግሎት የገቡ አዳዲስ ሆቴሎችን በተዘጋጀው መመሪያ መሰረት በደረጃ የመመደብ ተግባር ሊከናወን በተለይም ከቀረጥ ነጻ እቃዎችን አስገብተው

አገልግሎት መስጠት የጀመሩ አዳዲስ ሆቴሎ፣ች አገልግሎት በተቀመጠው አሰራር መሰረት ሥራ ከጀመሩ በአንድ አመት ውስጥ ሊመዘኑና ደረጃ ሊሰጣቸው ይገባል።

- በምዘና መመሪያው አስገዳጅ ተብለው የተቀመጡት መስፈርቶች በተለይ የእሳት አደጋ መከላከያ መስፈርቶች ሳይሟሉ ደረጃ መስጠት መቆም አለበት።
- በተጨማሪም የደረጃ ምደባ ከተከናወነ በኃላ ውጤቱ በተቻለ ፍጥነት የምደባው ውጤት ለተመዘነው ድርጅትም ሆነ ለህዝቡ ይፋ ሊደረጉ እና ውጤቱን ለማሳወቅ እስከ ሁለት አመት ድረስ የሚቆየው መዘግየትን ሊያስቀርና በተለያየ ምክንያት የሚያዘገይቱም ላይ የተጠያቂነት አሠራር ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል።
- የኮከብ ደረጃ የተሰጣቸው ሆቴሎች በዕቅድ ላይ የተመሰረተ በዓመት ሁለት ጊዜ የክትትል ሊደረግላቸው የሚገባና በተቀመጠው መስፈርት መሰረት በመሉ ሊገመገሙ፣ የክትትል ባለሙያዎቹም የክትትትሉ ውጤትን መሰረት በማድረግ የውሳኔ ሃሳብ ሊያቀርቡ እና በሚመለከተው አካል ጸድቆ ውሳኔ ሊሰጥና በውሳኔው መሰረት የማስተካከያ እርምጃ ሊወሰድ የሚገባና ይህን በማያሟሉ አካላት ላይም ተጠያቂ የሚደረጉበት አሠራር ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል። ከክትትል በተጨማሪ ሁሉም የኮከብ ደረጃ የተሰጣቸው ሆቴሎች ደረጃው ከተሰጣቸው ከሦስት ዓመታት በኋላ የዳግም ደረጃ ምደባ ስራ ሊከናወንላቸው እና ይህም በዕቅድ ሊደገፍ ይገባል።
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ቱሪዝም ልማት ዘርፍ የሚመለከታቸውን የግል፣ የፌዴራል እና የክልል መንግስት ተቋማትን በማስተባበር የኢትዮጵያ ቱሪዝም ቦርድ እንዲቋቋም ሊያደርግ ይገባል።
- በተጨማሪም ከሚመለከታቸው የፌዴርልና የክልል ባለድርሻዎች፣ ከግል ባለሀብቱ እና ከአለም አቀፍ ተቋማት ጋር በትብብር የሚሰራበትን የአሰራር ማእቀፍ ሊዘረጋ፣ ዘርፉን ለማገዝ የተፈቀዱ የቀረጥ ነጻ መብቶች ለተባለላቸው ዓላማ መዋላቸውን ሊያረጋግጥና እንዲሁም ቱሪስቶች በሚሄዱባቸው ሥፍራዎች ሁሉ ተገቢውን አገልግሎት የሚያገኙበትንና የቱሪስት ፍሰቱ የሚጨምርበትን ሁኔታ በማመቻቸት በቱሪዝም ዘርፍ ለማሳካት የታቀደውን ከግብ ሊያደርስ ይገባል።

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. ቱሪዝም ሰዎች ከሚኖሩበት አካባቢ በጊዜያዊነት በመነሳት ወደሌሎች አካባቢዎችና ሀገራት በመሄድ ታሪካዊና ባሕላዊ ኩነቶችን የሚታደሙበት፤ እንዲሁም ተፈጥሯዊና ሰው-ሰራሽ ገጽታዎችንና ክስተቶችን የሚጎበኙበት ኢንዱስትሪ ነው። ይህ ኢንዱስትሪ እጅግ ጠቃሚውና ከማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ቀጥሎ በዓለም ላይ በፍጥነት በማደግ ላይ የሚገኝ ሴክተር መሆኑን መረጃዎች ይጠቁማሉ። እንዲሁም ቱሪዝም በዓለም ኢኮኖሚ የላቀ ድርሻ ከሚሰጣቸው ዘርፎች አንዱ ነው። ዘርፉ በሀገር ኢኮኖሚ ውስጥ የስራ እድልን በመፍጠርና የውጭ ምንዛሬን በማስገኘት ረገድ ትልቅ ሚና ያለው ነው። በመሆኑም የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ቱሪዝም ያለውን አስተዋጽኦ በመረዳት በአለም አቀፍ፣ በአህጉርና በቀጠና ደረጃ ተፈጻሚ የሚሆኑ እቅዶችና ስምምነቶችን አድርጓል።

2. ከዚህ ጋር በተያያዘ ኢትዮጵያ በ United Nations Educational, Scientific and Cultural Organization (UNESCO) ቅርስነት የተመዘገቡ ልዩ ልዩ የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ የቱሪዝም መስህቦች ባለቤት ስትሆን፤ እነዚህን የቱሪዝም መስህቦች ለመጎብኘት በየጊዜው የሀገር ውስጥ ጎብኝዎችን ጨምሮ ከተለያዩ ክፍላተ-ዓለም ጎብኝዎች ወደ ሀገሪቷ የሚመጡ ሲሆን፣ ይህም የሀገርን ታሪካዊ፣ ባሕላዊና ተፈጥሯዊ ገጽታን ከማስተዋወቅ ባለፈ ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ እያስገኘ ይገኛል።

3. ለአብነትም እ.ኤ.አ በ2018 እና በ2021 ኢትዮጵያ ወደ 7.4 እና 2.6 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር (እንደ ቅደም ተከተላቸው) ከቱሪዝም ዘርፍ ማግኘት መቻሉን ከዓለም የቱሪዝም ድርጅትና World Data.Info የተገኙ መረጃዎች ይጠቁማል።

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ ታሪካዊ ዳራ

4. የኢትዮጵያ ቱሪዝም ሚኒስቴር በተለያየ የስያሜና የአደረጃጀት ለውጥ ሂደት ውስጥ ያለፈ ሲሆን፤ በዚህም መሰረት እስከ 1997 ዓ.ም ድረስ "የቱሪዝም ኮሚሽን" ተብሎ ይጠራ እንደነበርና በ1997 ዓ.ም እንደ አንድ ዘርፍ ሆኖ "የባሕልና ቱሪዝም ሚኒስቴር" በሚል ስያሜ በሚኒስቴር መ/ቤት ደረጃ አዋጅ ቁ.471/98 ተቋቋመ።

5. በ2014 ዓ.ም ቱሪዝም ለአገሪቱ ኢኮኖሚ ከፍተኛ አስተዋጾ እንደሚያበረክት ለብቻው ቢደራጅ የተሻለ መሆኑ ስለታመነበት የአስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባራት ለመወሰን በወጣ አዋጅ ቁጥር 1263/2014 የቱሪዝም ሚኒስቴር በመባል ተደራጀ፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ ራዕይ እና ተልዕኮ

### ራዕይ

6. የሚኒስቴሩ ራዕይ "በ2022 ዓ.ም የቱሪዝም ዘርፍን በማላቅ ከቀዳሚየአገር ብልጽግና መሰረቶች አንዱ ማድረግ" የሚል ነው።

### ተልእኮ

7. "የአገራችን ታሪካዊና ተፈጥሯዊ የቱሪዝምን ሃብቶች በማጥናት በህብረተሰቡ ተሳትፎ በባለድርሻ አካላት ቅንጅት በመጠበቅ፤ በማልማት፤ በማስተዋወቅና የአገራችንን መልካም ገጽታ በመገንባት ዘላቂና ተወዳዳሪ የቱሪዝም ኢንዱስትሪ መፍጠር እና የላቀ ማህበራዊ፣ ምጣኔ ሃብታዊ እና ስነ-ምህዳራዊ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ" ነው፡

## የቱሪዝም ሚኒስቴር ሥልጣንና ተግባራት

8. የአስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣ አዋጅ ቁ.1263/2013 መሰረት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ለቱሪዝም ሚኒስቴር ተሰጥተዋል፡

ሀ) የቱሪዝም ልማትና ተወዳዳሪነትን በቀጣይነት የሚያረጋግጡ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችንና የሕግ ማዕቀፎችን ያመነጫል፣ ለአፈጻጸሙ ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርሀ-ግብር ያዘጋጃል፤ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል

ለ) በቱሪዝም ዘርፍ ልማት የግል ዘርፉን ተሳትፎና ሚናን ለማሳደግ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ለአፈጻጸሙ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፣

ሐ) የሀገሪቱን የቱሪዝም እና የኢኮ-ቱሪዝም አለኝታዎችና መስህቦች በአግባቡ እንዲለዩና እንዲታወቁ ያደርጋል፣ ለቱሪዝም አመቺ ሆነው እንዲደራጁና እንዲለሙ ያደርጋል፤

መ) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ለቱሪዝም ጉብኝት እጅግ አስፈላጊ የሆኑ የቱሪዝም መዳረሻዎችን መሠረተ ልማት ይዘረጋል፣ ተጨማሪ አዳዲስ መሠረተ ልማቶች እንዲገነቡ ያደርጋል፤

ሠ) አዳዲስ የቱሪዝም መስህቦች እንዲለሙ ያደርጋል፣ የልማት ክፍተት ባለባቸው ቦታዎች የቱሪዝም መዳረሻዎች ያለማል፤ ነባር የቱሪዝም መዳረሻዎች እንዲጎለብቱ እና የቱሪዝም ምርት እና አገልግሎት በዓይነትና በመጠን እንዲያድጉ በማድረግ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ያደርጋል፣ የግል ባለሀብቶችም በልማቱ እንዲሳተፉ ያበረታታል፤

ረ) የተለያዩ የቱሪዝም ባለድርሻ አካላት የሚያከናውኗቸውን የቱሪዝም ገበያ ፍለጋና ማስተዋወቅ፣ የገበያ ትስስር እና ብራንዲንግ ሥራዎችን በማቀናጀትና በመምራት

የሀገሪቱን የቱሪዝም ሀብቶች፣ መስህቦችና መልካም ገፅታ በውጭ ሀገርና በሀገር ውስጥ በስፋት ያስተዋውቃል፤ አዳዲስ የቱሪዝም ገበያዎችን ይፈጥራል፣ የዘርፉን የገበያ ድርሻ እንዲያድግ ያደርጋል፤

ሰ) ዘርፉ በቴክኖሎጂ፣ በጥናትና ምርምር እንዲደገፍ እና ለሀገራዊ ኢኮኖሚ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ እንዲያድግ ያደርጋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

ሸ) የቱሪዝም መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያደራጃል፣ ያሰራጫል፤

ቀ) የሀገሪቱ የተፈጥሮ ቅርሶች እንዲጠኑ፣ እንዲጠበቁና ለቱሪዝም አመቺ ሆነው እንዲለሙና ጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚደረጉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

በ) በፌደራል መንግስት እንዲተዳደሩ የተሰየሙ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች በአግባቡ እንዲጠበቁ፣ ለቱሪዝም አመቺ ሆነው እንዲለሙና እንዲመሩ የማደረግ ሥራን ያስተባብራል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ስትራቴጂዎች እና ፕሮግራሞች ይቀርጻል፣ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፤

ተ) የሀገሪቱ የቱሪስት መስህቦች በዓለም አቀፍ ቅርስነት ለማስመዝገብ የሚያስችሉ ቅድመ ሁኔታዎችን በማሟላት የሚመዘገቡበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

ቸ) የሀገሪቱን የቱሪዝም መስህቦች፣ ምርትና አገልግሎቶች መለያ በመቅረጽና በየጊዜው በማሻሻል በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

ኀ) የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ደረጃዎች ይወስናል፣ ተፈጻሚነቱን ይቆጣጠራል፤

ነ) ሥልጣኑ በግልጽ በሌላ አካል ካልተሰጠ በስተቀር ከአንድ በላይ በሆኑ ክልሎች ውስጥ አገልግሎት ለሚሰጡ ወይም ሕግ በሚፈቅደው አግባብ በውጭ ባለሀብቶች ለሚካሄዱ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፤

ኘ) ከቱሪዝም ተዋናዮች ጋር አጋርነትና ትብብር በመፍጠር ይሰራል፤

አ) የመንግሥትና በቱሪዝም ዘርፍ የተሰማሩ የግል ዘርፍ አካላትን ያስተባብራል፣ ከክልል የቱሪዝም አካላት ጋር በጋራ የሚሰራበትን ማዕቀፍ በማዘጋጀት በሥራ ላይ ያውላል፤ ጥራት ያለው የቱሪዝም አገልግሎትና የቱሪስቶችን ደህንነት ለማረጋገጥ ያሉትን ዘርፈ-ብዙ ጥረቶች ለማስተባበር በቱሪዝም ዙሪያ የጋራ መድረክ ይፈጥራል፤

ከ) ሥልጣንና ተግባራቱን ለማስፈጸም እንዲያስችለው የሚቋቋመውን የቱሪዝም ፈንድ ያስተዳድራል፤

ኸ) የግል ዘርፍ አካላትንና የቱሪዝም ዘርፍ ልማት የሚመለከታቸው የፌደራል እና የክልል መንግስት ተቋማትን ለማስተባበር የኢትዮጵያ ቱሪዝም ቦርድ በሕግ የሚደራጅበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤


ወ) የቱሪዝም ዘርፍ መረጃ ሥርዓትን ይዘረጋል፤ ከፕላንና ልማት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የቱሪዝም ሳተላይት አካውንት በሀገራዊ የኢኮኖሚ አካውንት ሥርዓት ውስጥ ለማዋሃድ ሥርዓት ይዘረጋል፤

ገ/ በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች ለባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የተሰጡ ቱሪዝምን የሚመለከቱ እና ለቱሪዝም ኢትዮጵያ የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው ቱሪዝም ሚኒስቴር ተሰጥ ተዋል።

## የቱሪዝም ሚኒስቴር ድርጅታዊ አወቃቀር

9. የቱሪዝም ሚኒስቴር በአንድ ሚኒስቴርና በሁለት ሚኒስቴር ደኤታ የሚመራ ሲሆን የቱሪዝም ቦርድ፣ የቱሪዝም ሚኒስትር ጽ/ቤት፣ በ3 ዋና ሥራ አስፈጻሚዎች፣ በ7 መሪ ሥራ አስፈጻሚዎች እና በ9 ሥራ አስፈጻሚዎች ተደራጅቷል። **የሚኒስቴር መ/ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅር በአባሪ 1 ተያይዟል፡**

## የቱሪዝም መዳረሻና የመሰረተ ልማት የስራ ክፍል የስራ ፍሰት መግለጫ /Process Description/



## የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሰው ኃይል

10. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በመዋቅር ከተፈቀደለት 256 የስው ሃብት የስራ መደብ ውስጥ እስከ ታሕሳስ ወር 2017 በጀት ዓመት ድረስ በድምሩ 115 (45%) የሚሆነው የስራ መደብ በሰው ኃይል የተሸፈነ ሲሆን፤ አዲቱ የሚካሄድበት የቱሪዝም መዳረሻና መሰረተ ልማት ማስፋፊያ ዘርፍ በመዋቅር 41 የሰው ኃይል ተፈቅዶለት 19 (46%) የሚሆነው የስራ መደብ በሰው ኃይል ተሸፍኗል። የሚኒስቴሩ አጠቃላይ የሰው ኃይል ማስረጃ በፆታና በትምህርት ደረጃ እንደሚከተለው ተቀምጧል።

| የትምህርት ደረጃ | ሴት ብዛት | ወንድ ብዛት | ድምር |
|---|---|---|---|
| ዲፕሎማና ከዚያ በታች | 11 | 12 | 23 |
| ዲግሪ | 25 | 27 | 52 |
| ማስተርስ | 10 | 30 | 40 |
| ዶክትሬት | 0 | 0 | 0 |
| ድምር | 46 | 69 | 115 |

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ

11. የኢ.ፌዴ.ሪ ቱሪዝም ሚኒስቴር በ2014 ዓ.ም የአስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባራት ለመወሰን በወጣው ማቋቋሚያ አዋጅ ቁ.1263/2014 የተሰጡትን ተግባራትና ኃላፊነቶች ለመወጣት እንዲያስችለው ከመንግስት በጀት የሚመደብለት ሲሆን፤ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ በተገኘ ማስረጃ ከ2014-2017 ዓ.ም ታሕሳስ ወር ድረስ ያለው የበጀት አፈጻሙ እንደሚከተለው ተመላክቷል።

### መደበኛ በጀት

| የበጀት ዓመት | የጸደቀ መደበኛ በጀት (ብር) | ጥቅም ላይ የዋለ | አፈጻጸም በመቶኛ |
|---|---|---|---|
| **2014** | 94,640,596.00 | 73,327,220.05 | 77.48 % |
| **2015** | 206,213,830 | 202,046,044.21 | 97.98 % |
| **2016** | 231000870.00 | 198060219.09 | 93% |
| **2017** የ6 ወራት አፈፃፀም። | 180707870.00 | 86147513.59 | 48% |

### ካፒታል በጀት

| የበጀት ዓመት | የጸደቀ ካፒታል በጀት | ጥቅም ላይ የዋለ | አፈጻጸም በ% |
|---|---|---|---|
| 2014 | የለም | - | - |
| 2015* | 400,000,000 | 81,013,247.59 | 20.25%* |
| 2016 | 708881424.97 | 558881424.97 | 79% |
| 2017 የ6 ወራት አፈፃፀም። | 600000000.00 | 351250000.00 | 59% |

*የ2015 በጀት አመት የካፒታል ፕሮጀክት አፈጻጸም ዝቅተኛ የሆነው የጅማ አባጅፋር ቤተ መንግስት ለጥገና የተያዘ በጀት ሲሆን ነገር ግን በኮንትራክተሩ እና አማካሪ መሃንዲሱ መሰራት የነበራባቸዉ በወቅቱ ስላተሰራ ያልተከፈለ ቢሰሩ መከፈል የነበረበት ስላልተከፈለ ነው የሚል ምክንያት ቀርቧል።

## የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ

12. የቱሪዝም ሚኒሰቴር የቱሪዝም መዳረሻ ልማትና አገልግሎት አሰጣጥ ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ እየተከናወነ ስለመሆኑ በመገምገም በስራው ዙሪያ የአሰራር ክፍተቶች ካሉ በመለየት ችግሮቹን ለመቅረፍ ወይንም ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሀሳቦችን ማቅረብ እንዲሁም ተጠያቂነተን ለማስፈን ታስቦ የተከናዎነ ነው።

## የኦዲቱ ወሰን

13. ኦዲቱ የተከናወነው ለፌደራል ዋና ኦዲተር በአዋጅ ቁጥር 982/2008 ዓ.ም በተሰጠው ሥልጣንና በዓለም ዓቀፍ የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች መሰረት (International Performance Audit Standards) ሲሆን፣ ኦዲቱ በዋናነት በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ቱሪዝም ሚኒስቴር ከ2014- 2016 በጀት ዓመታትና የ2017 በጀት ዓመት አጋማሽ ድረስ ነው። በኦዲቱ በናሙና የተመረጡ የክልል የቱሪዝም መ/ቤቶች፣ ብሔራዊ ፓርኮችና የብሔራዊ ፓርክ ጽ/ቤቶች፣ እንዲሁም አጋርና ባለድርሻ አካላት የግምገማው አካል ተደርገዋል። **በናሙና ተመርጠው የታዮ አካላት ዝርዝር በአባሪ 3 ተያይዟል።**

## የኦዲቱ ዘዴ

14. ኦዲቱን ለማካሄድ የሰነድ ክለሳ የኦዲት ዘዴ ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን፤ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ማቋቋሚያ አዋጅ፣ ደንብ፣ በሚኒስቴሩ የተዘጋጁ የተለያዩ መመሪያዎች፣ በየሚኒስቴር መ/ቤቱ ዕቅድና አፈጻጸም ሪፖርቶች፣ የጥናት ሪፖርቶች ተከልሰዋል። በተጨማሪም ማስረጃ የመከለስና የመተንተን፣ የመስክ ምልከታና የቃለ-መጠይቅ የኦዲት ዘዴዎች ጥቅም ላይ ውለዋል። በአካል ተገኝቶ ቃለ-መጠይቅና ምልከታ ማድረግ ላልተቻለባቸው አራት ብሔራዊ ፓርኮች ቃለ መጠይቅ ተልኮላቸው ምላሻቸውን ሰጥተዋል።

## ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ

15. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ "በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የቱሪዝም ሚኒስቴር የቱሪዝም መዳረሻ ልማትና አገልግሎት አሰጣጥ አፈጻጸምን መገምገም" የሚል ነው።

## የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች

16. ከላይ በተገለጸው የኦዲት አካባቢ ሥር ሦስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች የተመረጡ ሲሆን እነሱም፡-

1. በቱሪዝም ሚኒስቴር የቱሪዝም መዳረሻ ስፍራዎች የመሰረተ ልማት መሟላቱን ለማረጋገጥ ቀልጣፋና ውጤታማ የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፤
2. ለቱሪስት አገልግሎት የሚሰጡ ሆቴሎች ደረጃ ምደባ በተመለከተ ቀልጣፋና ውጤታማ የክትትልና ቁጥጥር ስርአት ዘርግቶ ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፤
3. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የቱሪዝም መዳረሻ አካባቢዎችን ለማልማት ከሚመለከታቸው አጋርና ባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ መስራቱንና በቴክኖሎጂ የታገዘ መረጃ አያያዝና ልውውጥ እንዲኖር የሚያስችል ቀልጣፋና ውጤታማ ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ስለመደረጉ መገምገም፤

የሚሉ ናቸው።

## የኦዲት መመዘኛ መስፈርት

17. በኦዲት ቡድኑ የተመረጡትን ሶስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ለመመዘን የሚረዱ ሃያ አንድ (21) የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) ተዘጋጅተው ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ቀርበው አስተያየት እንዲሰጥባቸው ተደርጓል። **የኦዲቱ መመዘኛ መስፈርቶች በአባሪ 2 ተያይዘዋል።**

# ክፍል ሁለት

## የኦዲት ግኝቶች

### የቱሪስት መዳረሻ ሥፍራዎች መሰረተ ልማት እንዲሟላ የአሰራር ማዕቀፍ ዝግጅትን በተመለከተ

18. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በቱሪስት መዳረሻ ብሔራዊ ፓርኮች ላይ አስፈላጊ መሠረተ ልማት እንዲሟሉላቸው እንዲሁም ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመቀናጀት የአሰራር ማዕቀፎችን ሊያዘጋጅ እና አፈጻጸሙን ሊከታተል ይገባል፡፡

19. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በቱሪስት መዳረሻዎች ላይ ለሚካሄዱ የመሰረተ ልማት ግንባታዎች የመዳረሻ ልማት የአሰራር መመሪያ አለማዘጋጀቱን፤
- በቱሪስት መዳረሻ ሥፍራዎች ዘላቂ የቱሪዝም ኢንቨስትመንትን ለመተግበር የሚያስችል ማዕቀፍ አለመኖሩ፤
- መሰረተ ልማት ማሟላትን ያካተተ የ10 ዓመት የፓርክ አስተዳደር ፕላን (Park Management Plan) ያልተዘጋጀላቸው ብሔራዊ ፓርኮች መኖራቸው (ሀላይደጌ አሰቦት፣ ጋምቤላ፣ ነጭ ሳር እና ያንጉዲ ራሳ)፤
- ከሰሜንና ባሌ ብሔራዊ ፓርኮች ውጭ ለሌሎች 11 ብሔራዊ ፓርኮች የመሰረተ ልማት ማስተር ፕላን ያልተዘጋጀላቸው መሆኑን፣

ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች፣ ለተጠሪ ተቋማት፣ በናሙና ተመርጠው የታዩ ለክልል የቱሪዝም ቢሮዎች እናብሔራዊ ፓርኮች ከቀረበ መጠይቅ እና ከተከለሱ የሰነድ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

20. ጉዳዩን በተመለከተ የሚኒስቴሩ የስራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት አስተያየት የቱሪዝም መሰረተ ልማት ግንባታዎች በቱሪዝም መዳረሻዎች መሰረተ ልማት ስራዎቹ እንደየሚሰሩበት ቦታ የተለያየ መልክ ያለዉ መሆኑን ግለጽው፤ ለምሳሌ በብሔራዊ ፓርኮችና በከተሞች ወይም በተራራማ ቦታዎችና በሀይቆች የሚሰሩ መሰረተ ልማቶች የተለያየ ባህሪ ነዉ ያላቸዉ፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ እስከአሁን ድረስ በብሔራዊ ፓርኮች ለሚሰሩ የቱሪዝም መሰረተ ልማት መመሪያ/ስታንዳርድ ተሰርቶ የተጠናቀቀ ሲሆን በሌሎች ቦታዎች ለሚሰሩ መሰረተ ልማቶች ደግሞ በቀጣይ በአፋጣኝ የሚዘጋጅ ይሆናል ብለዋል፡፡

21. በተጨማሪም የፓርክ አስተዳደር ፕላን (General Park Management Plan) ያልተዘጋጀላቸው ተብለው በኦዲቱ የተገለጹት ብሔራዊ ፓርኮችን በተመለከተ

የኢትዮጵያ ዱር እንስሳት ጥበቃ ባለስልጣን ከGIZ ከተሰኘ የግብረ-ሰናይ ድርጅት ጋር በመተባበር የአለም አቀፉን የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ህብረት IUCN የፓርክ አስተዳደር ፕላን (General Park Management Plan) አዘገጃጀት መስፈርቶችን ተከትሎ የተዘጋጀላቸውና አሁን እተተገበረ ያለ ሲሆን የሀላይደጌ አሰቦት ብሔራዊ ፓርክም ይህንኑ መስፈርት ባሟላ መልኩ ተዘጋጅቶ ጸድቆ ስራ ላይ ለማዋል በመጨረሻው ምዕራፍ ላይ ይገኛል የሚል ምላሽ ሰጥተዋል።

22. የሚኒስቴሩ የስራ ኃላፊዎች ይህንን ይበሉ እንጂ፤ የፓርክ አስተዳደር ዕቅድ ተዘጋጅቶ ሥራ ላይ ውሏል ለተባሉትም ሆነ ለመጽደቅ በዝግጅት ላይ ናቸው ለተባሉት የፓርክ አስተዳደር ዕቅድ (Park General Management Plan) የሰነድ ማስረጃ ባለመቀርቡ እንዲሁም በኦዲቱ ለተጠቀሱት ብሔራዊ ፓርኮች የመሰረተ ልማት ማስተር ፕላን የተዘጋጀላቸው ስለመሆኑ ወይም ለምን እንዳልተዘጋጀላቸው ምላሽ ባለመሰጠቱ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ይቸግራል።

23. በመሆኑም ለቱሪስት መዳረሻ ብሔራዊ ፓርኮችና ቅርሶች የተዘጋጀው የፓርክ አስተዳደር ዕቅድና ማስተር ፕላን አለመኖር በመዳረሻ ስፍራዎች ያልተሟሉ የመሰረተ ልማት አውታሮችን ለሚሟላት የተበላሹትንም በአፋጣኝ በመጠገን ያሉባቸውን የመሰረተ ልማት ችግሮች በዕቅድ ላይ ተመስርቶ ለመቅረፍ እና ፓርኮቹ ሆኑ ሌሎች መዳረሻዎች ደረጃቸውን የጠበቁና ተወዳዳሪ የቱሪስት መዳረሻ በማድረግ ጎብኝዎችን አስደሳች በማድረግ ቆይታቸውን በማራዘም ወይም ድጋሚ እንዲመጡ ማድረግን አዳጋች ያደርገዋል።

## የቱሪዝም ኢንቨስትመንት ለማበረታታት ጥናት መከናወኑን በተመለከተ

24. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የቱሪዝም ኢንቨስትመንትን ለማሳደግ ማነቆ የሆኑ አሰራሮችን እና የህግ ማዕቀፎችን በጥናት በመለየት እና ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመተባበር እንዲሻሻሉ ሊያደርግ፤ አዳዲስ ማዕቀፎች እንዲዘጋጁና በስራ ላይ እንዲውሉ ሊያደርግ እንዲሁም አፈጻጸማቸውን ሊከታተል ይገባል።

25. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-

- ከ2014 ዓ.ም እስከ 2018 ዓ.ም ድረስ ባሉት ዓመታት ለመተግበር ታስቦ የቱሪዝም ኢንቨስትመንት ስትራቴጂ ሰነድ በ2014 ዓ.ም የተዘጋጀ ቢሆንም፤ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት (እስከ ጥር 2017 ዓ.ም) ጊዜ ድረስ ያልፀደቀ እና የመተግበሪያ ጊዜው ሊጠናቀቅ ወራት የቀሩት መሆኑ፣

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በጥር 2016 ዓ.ም በቱሪዝም ኢንቨስትመንት ዘርፍ ያሉ ክፍተቶችን በተመለከተ /Ethiopian Tourisim Investment Gap Analysis/ ጥናት አከናውኗል። በጥናቱ ላይ ከተጠቀሱ ክፍተቶች ውስጥ፡-
    - ለቱሪዝም ኢንቨስትመንት ሊውሉ የሚገባቸውን የመዳረሻ ስፍራዎች ለይቶ የመከለል ስራ ያልተከናዎነ /Lack of Tourism Investment Zoning or Mapping/ ፤
    - በቱሪዝም ኢንቨስትመንት ዘርፍ ለኢንቨስተሮች የአንድ መስኮት አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት አለመዘርጋቱ፣
    - በመንግስት የኢንቨስትመንት ባለድርሻ አካላት ዘንድ በዘርፉ በግልጽ የተለየ ኃላፊነት አለመኖሩ፤
    - በቱሪዝም ኢንቨስትመንት ዘርፍ ያለው የክትትልና ግምገማ ስርዓት ውጤታማ አለመሆኑን፤
    - በቱሪዝም ኢንቨስትመንት ዘርፍ የሚሰጡ ማበረታቻዎች ለታለመላቸው ዓላማ ያልዋሉ መሆናቸውን ሲረጋገጥ የእርምት እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት አለመኖሩ፤
    - በቱሪዝም ኢንቨስትመንት ዘርፍ የባለድርሻ አካላት ቅንጅት ደካማ መሆኑን፤
    - የኢንቨስትመንት ፈቃድና ማበረታቻ ሥርዓቱ ተግባራቱን በፌዴራል ደረጃ ብቻ እንዲከናዎኑ የሚፈቅድ መሆኑ ነገር ግን ክልሎች ይህንኑ ተግባር እንዲያከናውኑ የማይፈቅድ መሆኑ፤
    - በቱሪዝም ኢንቨስትመንት ዘርፉ የሚደረጉ ማበረታቻዎች ውጤታማ ስለመሆናቸውና ያመጡትን ለውጥ ለማረጋገጥ መደበኛ በሆነ መልኩ ግምገማ የማይደረግ መሆኑ፤
    - በቱሪዝም ኢንቨስትመንት ዘርፍ ደካማ የመረጃ አስተዳደር ስርዓት መኖሩ በዘርፉ ማስረጃን መሰረት ያደረገ ውሳኔ ለመስጠት ተግዳሮት የፈጠረ መሆኑ፤
    - በቱሪዝም ኢንቨስትመንት ዘርፍ ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር ያለው ቅንጅት ደካማ ሰለመሆኑ የተገለጸ መሆኑ፤
- የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ህጎችና መመሪያዎች ክፍተት ያለባቸው መሆኑ፤ ለአብነትም፡- ሥርዓቱ ከከተማ ርቆ በሚገኙ መዳረሻዎች ኢንቨስት ለሚያደርጉ ባለሀብቶች የተለየ ማበረታቻ የማይፈቅድ መሆኑ፤
- ከቀረጥ ነፃ የሚፈቀዱ ተሸከርካሪዎች የሀገሪቱን አካባቢያዊ ሁኔታና የቱሪስቶችን ምቾት ከግምት ውስጥ ያላስገባ መሆኑ፤ በመዳረሻ አካባቢዎች ለቱሪስት ካምፒንግ ግብዓት የሚሆኑ እና ለባሕል ቤቶች የሙዚቃ መሳሪያ የቀረጥ ነጻ ማበረታቻ ሕጉ ያላካተታቸው መሆኑ፤

- ለቱሪዝም ኢንቨስትመንት ሊውሉ የሚገባቸውን የመዳረሻ ስፍራዎች ለይቶ የመከለል ስራ ያልተከናዎነ መሆኑ /Lack of Tourism Investment Zoning or Mapping/፤

- በሲዳማ ክልል በአገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች ዘርፍ (በሆቴል፣ የእንግዳ ማረፊያ፣ ሎጂ፣ የባሕል ቤቶች...ዘርፍ) ክፍተት የሚስተዋልባቸውን የክልሉ አካባቢዎች በጥናት የመለየት ስራ አለመሰራቱን፣

በናሙና ለተመረጡ የክልል የቱሪዝም ቢሮ የስራ ኃላፊዎች ከቀረበ መጠይቅና ከተከለሱ የሰነድ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል።

26. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው፤ የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ሕጉ ወጥነት ያለው በመሆኑና ልዩ የኢንቨስትመንት ማበረታቻ የሚሹ አካባቢዎችን ከግምት ውስጥ ያላስገባ በመሆኑ፤ በዘርፉ ኢንተርፕራይዞችን አደራጅቶ ወደ ስራ እንዲገቡ ለማድረግ የፋይናንስ እጥረት በመኖሩና በግል ኢንቨስተሮች በኩል ከከተማ ውጪ ራቅ ወዳሉ መዳረሻ አካባቢዎች ኢንቨስት ለማድረግ ቁርጠኝነት የሌለ መሆኑ እንደ ምክንያት ሊወሰድ እንደሚችል ገልጸዋል።

27. እንዲሁም የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ለተላከላቸው የነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ፤

  - በቱሪዝም ኢንቨስትመንት ዘርፍ ያሉ የልማት ማነቆዎችን ከመቅረፍና እንዲሻሻሉ ከማድረግ አንጻር የዘርፉን ክፍተቶች ማጥናትና ለይቶ ለልማት ዝግጁ መሆን የዘርፉን የልማት እድሎች እና ተግዳሮቶችን እና ነባራዊ ሁኔታዎችን መተንተን እንደሚያስፈልግ፣

  - የቱሪዝም ዘርፍ የኢንቨስትመንት ክፍተቶች የተለዩ ሲሆን ለተግባራዊነቱም ምንም እንኳን ለሁሉም ክፍተቶች 100% ምላሽ የተሰጠ ባይሆኑም ችግሩን መፍታት የሚያስችሉ እና 80% ለችግሩ መፍቻ የሚሆኑ የማዕቀፎች ዝግጅትና ስትራቴጂክ ስራዎች ማለትም (የቱሪዝም ኢንቨስትመንት ስትራቴጂ ተዘጋጅቶ ወደስራ የማስገባት እንቅስቃሴ መጀመሩን፤

  - የተለያዩ ባለሀብቶችን ለመሳብ የቱሪዝም ዕምቅ ሀብትና አዋጭነት የሚያሳይ ማስተዋወቂያ ሰነድ (Investment Pitch) መዘጋጀቱንና በተለያየ መንገድ የሀገሪቷን የቱሪዝም ኢንቨስትመንት አማራጮች የማስተዋወቅ ስራ በመሰራት ላይ መሆኑን፤ እንዲሁም የቱሪዝም ኢንቨስትመንት ፕሮፋይል መዘጋጀቱን፤ ህትመቱን እና በሶፍት ኮፒ የማሰራጨት ስራ በመከናወን ላይ የሚገኝ መሆኑን፣

- በተጨማሪም በቱሪዝም ኢንቨስትመንት ዘርፍ ለተሰማሩ ባለሀብቶች የሚሰጥ ማበረታቻ በአግባቡ ለታለመለት ዓላማ መዋሉ የሚገመገም መሆኑንና ለታለመላቸው ዓላማ ያልዋሉ መሆናቸው ሲረጋገጥ ለሚመለከታቸው አካላት የማሳወቅ ስራ የሚከናወን መሆኑን

ገልጸዋል።

28. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ይህን ምላሽ ቢሰጡም በምላሽ ላይ የተገለጹት ነጥቦች ዘርፉን ለማሻሻል በአጠቃላይ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ስራዎች እየተከናወኑ እንደሚገኙ የሚገልጹ እንጂ ከላይ በኦዲቱ የተለዩ ክፍተቶችን ስለመቀረፋቸው በማስረጃ የሚያረጋግጡ ስላልሆኑ፣ የቱሪዝም ኢንቨስትመንት የሚሰጡ የማበረታቻ ስርዓቶችን በተመለከተ ክትትል በማድረግ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ስለመደረጉም የሰነድ ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል።

29. በቱሪዝም ኢንቨስትመንት ዘርፍ በኦዲቱ የተጠቀሱት ማነቆዎች መኖራቸው፤ ዘርፉ እንደ ሀገር ሊያበረክት የሚችለውን የስራ ዕድል ፈጠራና የውጭ ኢንቨስትመንትን በመሳብ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ እንዳይቻል ያደርጋል።

## የቱሪስት መስህብና መዳረሻ ቦታዎች ማሟላት ያለባቸውን የመሰረተ ልማት ስታንዳርድ ስለመዘጋጀቱ በተመለከተ

30. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የቱሪስት መስህብ ሥፍራዎች ማሟላት ያለባቸውን መሰረተ ልማቶች የተመለከቱ ስታንዳርዶች እንዲዘጋጁ፣ በሚመለከታቸው አካላት በስራ ላይ እንዲውሉ ሊያደርግና ለአፈጻጸማቸው ድጋፍና ክትትል እንዲሁም በአግባቡ መተግበራቸውን ሊቆጣጠር ይገባል።

31. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፦

- ሆቴሎች ማሟላት ያለባቸውን መስፈርትና ባሟሉት መስፈርት የሚመደቡበት የኮከብ ደረጃ የሚገልጽ በኢትዮጵያ ደረጃዎች አገልግሎት (የቀድሞ ኤጀንሲ) በግንቦት 2006 ዓ.ም (May 2014) የወጣ መሆኑ፤
- በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኩል በእ.ኤ.አ 2024 በብሔራዊ ፓርኮች የሚያስፈልጉ መሰረተ ልማትና አገልግሎቶችን በተመለከተ ስታንዳርድ /Tourism Facilities and Infrustracture Needed in National Parks in Ethiopia የተዘጋጀ ቢሆንም በሚመለከተው አካል የጸደቀ ስለመሆኑ ማረጋገጫ የሌለው መሆኑ፤
- በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኩል የተዘጋጀና የጸደቀ የቱሪስት መስህብ ሥፍራዎች ማሟላት ያለባቸውን መሰረተ ልማቶች የሚገልጽ ስታንዳርድ አለመዘጋጀቱን፤

በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ሰነዶች፣ በናሙና ተመርጠው ቃለ-መጠይቅ የቀረበላቸው የኦሮሚያ፣ ሲዳማ ክልል እና አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቱሪዝም ቢሮዎች እንዲሁም የሚኒስቴሩ ተጠሪ ተቋማት የሆኑት ዱር እንስሳ ጥበቃ ባለሥልጣን እና የቅርስ ጥበቃ ባለስልጣን የስራ ኃላፊዎች ገልጸዋል።

32. ጉዳዩን በተመለከተ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት አስተያየት፤ በሃገሪቱ የሚገኙ የቱሪዝም መስህብና መዳረሻዎችን የልማት ደረጃ ለመለየት እንዲረዳ ሀገር አቀፍ የቱሪዝም መስህብ ልማት ስታንዳርድ (tourism attraction development index) መዘጋጀቱን፣ ሆኖም ግን ስታንደርዱን በየደረጃው ካሉ የባለድርሻ አካላት ጋር መወያየት የሚያስፈልግ በመሆኑ ከነባራዊ ሁኔታዎች ጋር የተጣጣመ ምክክር በማድረግ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በኩል ወደ ሥራ የሚገባ ይሆናል የሚል ምላሽ ሰጥተዋል።

33. በመሆኑም የቱሪስት መስህብ ማሟላት የሚገባቸው ስታንዳርድ በሁሉም ዘርፍ ተዘጋጅቶ ወደ ስራ አለመግባቱ እንደ ሀገር ወጥነት ያለው የመዳረሻ ልማት ስራ ማከናወንና በሁሉም መዳረሻ ደረጃውን የጠበቀ አገልግሎተር እየተሰጠ መሆኑን ማረጋገጥ እንዳይቻል ያደርጋል።

## የብሔራዊ ፓርኮች የመሰረተ ልማት ስታንዳርድ ዝግጅትን በተመለከተ

34. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ብሄራዊ ፓርኮች ሊያሟሉ የሚገባውን መሰረተ ልማትና አገልግሎት የሚገልጽ ስታንዳርድ በማዘጋጀት አፈጻጸሙን ሊከታተል ይገባል።

35. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፦

- ፓርኮች ብሔራዊ ፓርክ ለመባል ሊያሟሉ የሚገባውን መስፈርቶች፣ የመሰረተ ልማትና መስጠት ያለባቸው አገልግሎትን የሚገልጽ ስታንዳርድ ያልተዘጋጀ መሆኑ፤
- አለም አቀፍ ስታንዳርዶችን ያሟሉ የቱሪዝም መዳረሻዎችን ከመመስረት አንጻር (መሰረተ ልማትና ፋሲሊቲዎችን ለቱሪስቶች ከማሟላት አንጻር) ሰፊ ውስንነት ያለ መሆኑን፤
- የስንቅሌ ቆርኬዎች መጠለያ እና የአብጃታ ሻላ ብሔራዊ ፓርኮች፤ እንዲሁም የኢትዮጵያ ዱር እንስሳ ጥበቃ እና ቅርስ ጥበቃ ባለስጣን መ/ቤቶች በኦዲት ወቅት ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት ምላሽ ብሔራዊ ፓርኮችና ቅርሶች ሊያሟሉ የሚገባቸውን የመሰረተ ልማት አገልግሎት የሚገልጽ ስታንዳርድ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኩል ተዘጋጅቶ ያልደረሳቸው መሆኑን ለተጠቀሱት ብሔራዊ ፓርኮችና

ባለድርሻ አካላት የስራ ኃላፊዎች ከቀረበ ቃለ-መጠይቅና ከተከለሱ የሰነድ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል።

36. ጉዳዩን በተመለከተ የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት የስራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት አስተያየት፤ በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች የሚሰሩ መሰረተ ልማቶችና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሚከናወኑት የተለያዩ ስታንዳርዶችን በመከተል (የሥርዓት-አያያዝ ዕቅድ /General Management Plan/፣ በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች የሚቋቋሙ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ፣ የዱር እንሰሳት ጥበቃ ቦታዎች መሠረተ ልማት ግንባታ ማስተር ፕላን፣ ዝርዝር ዲዛይን መሰረት የሚተገበር መሆኑን ገልጸዋል።

37. ይሁን እንጂ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች በኩል ከላይ የተጠቀሱት ነጥቦች፡- /የሥርዓት-አያያዝ ዕቅድ/ በመዳረሻ ስፍራዎች የመሰረተ ልማት ክፍተቶችን ጨምሮ በሂደት ለማሟላት የተዘጋጀ የረዥም ጊዜ (10 ዓመት) ዕቅድ እንጂ ብሔራዊ ፓርኮች ሲቋቋሙ ከመሰረተ ልማትና ፋሲሊቲ አኳያ ሊያሟሉ የሚገባውን አገልግሎት ምን መምሰል እንደሚገባው የሚገማሟሟላት የሚገባው መስፈርት ወይም ስታንዳርድ ባለመሆኑ፣ የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያም ፓርኮቹ ውስጥ ለመስራት ለሚፈልጉ ተቋማት እንደ መስፈርት የሚያገለግል እንጂ ብሔራዊ ፓርኮች ሲቋቋሙ ከመሰረተ ልማትና ፋሲሊቲ አኳያ ሊያሟሉ የሚገባውን አገልግሎት የሚገልጽ ስታንዳርድ ባለመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም።

38. በመሆኑም ብሄራዊ ፓርኮች ከመቋቋማቸው በፊት ሊያሟሉ የሚገባ ግልጽ የሆነ መስፈርት እና በቅድሚያ መሰራት የሚገባውን መሰረተ ልማትና አገልግሎት የሚገልጽ ስታንዳርድ አለመዘጋጀቱ ፓርኮቹ ስማቸውንና ደረጃቸውን የሚመጥን አገልግሎት እንዳይሰጡ እና ለማሻሻልም ከመሰረተ ልማት አኳያ ያሉበትን ደረጃ መገምገም እንዳይቻል ያደርጋል።

## የቱሪስት መዳረሻ የመሰረተ ልማት የተሟላላቸው መሆኑንና የክፍተት ጥናትን መከናወኑን በተመለከተ

39. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በቱሪስት መዳረሻዎች የሚስተዋሉ የመሰረተ ልማት ክፍተቶች በሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባባር በጥናት ሊለይ እንዲሁም የተለዩትም ክፍተቶች ዕቅድ ተዘጋጅቶላቸው በሚመለከታቸው አካላት ሊሟሉ እና ሚኒስቴር መ/ቤቱም ችግሮቹ መቀረፋቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል።

40. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-

- በቱሪስት መዳረሻ ስፍራዎች የመሰረተ ልማት ክፍተቶችን በውስጡ የያዘ ጥቅል ጥናት በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኩል በየጊዜው ይከናውናል። ነገር ግን በጥናቱ የተለዩ ክፍተቶችን ለመቅረፍ ወደ ተግባር ለመግባት ዕቅድ ያልተዘጋጀ እና ጥናቱን ከመተግበር አኳያ ክፍተት መኖሩን፤
- የቱሪዝም መዳረሻ ስፍራዎች ወሳኝና ደጋፊ የመሰረተ ልማት ችግር ያለባቸው መሆናቸውን፤ ለአብነትም፡-
    - የመንገድ፣ የኤሌክትሪክ ኃይል፣ የውኃ አቅርቦት እና የቴሌኮሙኒኬሽን አቅርቦት ችግር መኖሩን፣
    - በአዋሽ ብ/ፓርክ ዉስጥ ዉሃ እና የኢንተርኔት አገልግሎት የሌለ መሆኑን፤
    - በገራሲሌ ብሔራዊ ፓርክ የፓርኩ ጽ/ቤትና አዉትፖስቶች /Outpost ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ የኤሌክትሪክ ሀይል ተጠቃሚ አለመሆናቸውን፡
    - በ2016 በጀት ዓመት በስንቅሌ ቆርኬዎች መጠለያ ፓርክ የጽ/ቤት አጥር ለመገንባት ታቅዶ የነበረ ቢሆንም አለመፈጸሙን በፓርኩ የ2016 በጀት ዓመት አፈጻጸም ሪፖርት ላይ መጠቀሱ፤
    - የጢያ ዓለም-ዓቀፍ ቅርስ እራሱን የቻለ ፅ/ቤት የሌለው መሆኑ፣
    - በባሌ ብሔራዊ ፓርክ የቢሮ ጥበት ችግር መኖሩን
    - በኦሞ ብሔራዊ ፓርክ የወንዝ ድልድይ አለመኖር (በዋናው ጽ/ቤት የሰራተኞች መኖሪያ አካባቢ ሙይና ዞንግዥ ወንዝ)፣ የሬንጀሮች መኖሪያ ቤት ጥገና እና የእሳት አደጋ መከላከያ መስመርን ለመስራት በበጀት ዓመቱ (2016 ዓ.ም) ታቅዶ አለመከናዎኑ፤
    - በደቡብ ሕዝቦች ክልል ኮንሶ የእርከን ስራና መኖሪያ መንደር የውሃ እጥረት በመኖሩ የጎብኝዎችን ቆይታ እያሳጠረ የሚገኝ መሆኑ፤
    - የቱሪዝም ሚኒስቴር የመካከለኛ ዘመን ዕቅድ (2016-2018 ዓ.ም) የዓለም አቀፉን የጉዞና ቱሪዝም ተወዳዳሪነት አመላካችን (Travel and Torurism development index) ጠቅሶ በ2015 ዓ.ም ባወጣው ሪፖርት፤ ኢትዮጵያ ከ148 ሀገራት መካከል በቱሪስት አገልግሎት መሰረተ ልማት ጥራት 138ኛ ደረጃ ላይ የምትገኝ መሆኑን መገለጹ፤
    - በዱር እንስሳ ጥብቅ ስፍራዎች የመሰረተ ልማት ሽፋን በተለይም የመንገድ አውታር ዝርጋታ እና የቱሪስት ፋሲሊቲ አቅርቦት ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የመካከለኛ ዘመን ዕቅድ (ከ2016-2018 ዓ.ም) ላይ የተጠቀሰ ቢሆንም ችግሩ በኦዲቱ ወቅትም የታየ መሆኑ፤

- በአብጃታ ሻላ ሐይቆች ብሔራዊ ፓርክ የሰራተኞች መኖሪያ ቤት እና የቢሮ እጥረት መኖሩን፤ ደረጃውን የጠበቀ የሬንጀሮች ቢሮ አለመኖሩ፣ ውሃ በፓርኩ ውስጥ ባለመኖሩ በተሽከርካሪ በማመላለስ የሚጠቀሙ መሆኑ፤ የመብራት ችግር መኖሩ፤ ለፓርኩ ደረጃውን የጠበቀ ጽ/ቤት፣ መንገድ፣ የሬንጀር አውትፖስት፣ መጸዳጃ ቤትና ሻዎር አገልግሎት፤ የቱሪስትም ሆነ የእንግዳ ማረፊያ አለመኖሩን፤ እንዲሁም ለጎብኝዎች የሚያገለግል ካምፕ ሳይት የሌለ መሆኑ፤




*ምስል ቁ.1፡ በአብጃታ ሻላ ሐይቆች ብሔራዊ ፓርክ የሚገኝ የቱሪስት መጸዳጃ አገልግሎት መስጫ*

- ብሔራዊ ፓርኮች ጎብኝዎች የሚያርፉባቸው፣ የሚመገቡባቸውና የሚዝናኑባቸው ሎጆች፣ ኢኮ-ሎጂዎች፣ ደረጃቸውን የጠበቁ የካምፕ ፋሲሊቲዎች የሌላቸው መሆናቸውን በሚኒስቴሩ የመካከለኛ ዘመን ዕቅድ (2016-2018) ላይ የተገለጸ መሆኑ፤

- በጋምቤላና ሀላይደጌ ብሔራዊ ፓርኮች ለጎብኝዎች የሆቴልና ማረፊያ አገልግሎት የሚሰጥ የቱሪስት አገልግሎት ሰጭ ድርጅት አለመኖሩን፤

- በአፋር ክልል በቱሪዝም መዳረሻ ቦታዎችም ሆነ በክልሉ ዋና ከተማ ጎብኝዎችን እያዝናኑ ሊያቆዩ የሚችሉ የኮከብ ደረጃ ያላቸው ሆቴሎች አለመኖራቸውን፣ በጋምቤላ ክልል የቱሪስት መዳረሻዎችን ከማልማት አኳያ ባለሀብቶች የኮከብ ደረጃ ያላቸው ሆቴሎች እንዲገነቡ ከማድረግ አኳያ ክፍተት መኖሩን፣

- በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች አስደናቂ ፈርጀ ብዙ የቱሪዝም መስህቦች የሚገኙ ቢሆንም መሰረታዊ የማረፊያና መመገቢያ ፋሲሊቲዎች ያልተሟላቸው መሆናቸውን ከሚኒስቴሩ የመካከለኛ ዘመን ዕቅድ (2016-2018) ላይ የተገለጸ መሆኑ፤

- በቱሪስት መስህቦች መካከል ያለው ርቀት በየብስ ለመጓዝ ረጅም ሰዓታትን የሚፈጅ በመሆኑ ጎብኝዎች በመሃል የሚያርፉባቸው የቱሪስት ፋሲሊቲዎች /Stop Over Tourist Facility/ አለመኖራቸው፤

- በነባር መስህቦች ቱሪስቶችን ለመሳብ ካላቸው ሰፊ እድል አንጻር የሆቴሎችና የአገልግሎት ሰጭ ተቋማት መጠንና የማስተናገድ አቅም ዝቅተኛ መሆኑን ከሚኒስቴሩ የመካከለኛ ዘመን ዕቅድ (2016-2018 ዓ.ም) ላይ የተጠቀሰ መሆኑ፤ (እንደ ሀገር የቱሪስት አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች/ፋሲሊቲዎች ቁጥር የመኝታ ክፍሎች ብዛት ከ20 ሽህ ያልዘለለ፤ እንዲሁም የአልጋ ብዛት ከ30 ሺህ ያልዘለለ መሆኑን፣ (ከሚኒስቴሩ የመካከለኛ ዘመን ዕቅድ (2016-2018 ዓ.ም) ላይ የተገለጸ መሆኑ)፤

- በጋምቤላ ክልል በ2015 በጀት ዓመት የሀገር ውስጥ እና የውጭ ኢንቨስትመንትን ማስፋፋትና ማሳደግ ግብ ስር ዝግጅት አጠናቀው አገልግሎት መስጠት የጀመሩ ባለሃብቶች ብዛትን በቁጥር 36 ለማድረስ ታቅዶ አፈጻጸሙ 12 /33.33%/ መሆኑ እንዲሁም በክልሉ በ2015 በጀት ዓመት የሀገር ውስጥ እና የውጭ ኢንቨስትመንትን ማስፋፋትና ማሳደግ ግብ ስር 3 የውጭ ሀገር ኢንቨስተሮችን/ ባለሀብቶችን ለመሳብ ታቅዶ አፈጻጸሙ 0 መሆኑን፤

በኦዲት ወቅት ከተከለሱ የሰነድ ማስረጃዎች ለማዎቅ ተችሏል።

41. ጉዳዮን በተመለከተ የሚኒስቴሩ የስራ ኃላፊዎች በዝርዝር ኦዲት ማጠቃለያ ተጠይቀው፤ ከላይ በኦዲቱ ለተጠቀሱት ነጥቦች ምክንያቱ ከከተማ ርቀው በሚገኙ መዳረሻ ስፍራዎች የግሉ ባለሀብቶች ኢንቨስት ለማድረግ ተነሳሽነቱ የሌላቸው በመሆኑና የግል ባለሀብቱን መሳብ ባልተቻለባቸው የቱሪስት አገልግሎት ሰጭ ተቋማት ክፍተት በሚስተዋልባቸው ስፍራዎች የመንግስት ኢንቨስትመንት ደካማ በመሆኑ ነው የሚል ምላሽ ሰጥተዋል።

42. እንዲሁም የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት የስራ ኃላፊዎች የቱሪስት አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች ቁጥርን በተመለከተ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት ምላሽ፤ በአሁኑ ወቅት የተሻለ የመኝታ ክፍሎችና አልጋዎች ቁጥር ያለ መሆኑን፤ ትክክለኛ ቁጥሩና ደረጃው በቀጣይ በጥናት ተለይቶ የሚገለጽ መሆኑን ገልጸው፤ ጎብኝዎች በመሀል በመዳረሻዎች መሀል የሚያርፉባቸውን ፋሲሊቲ ችግር ለመፍታት አስፈላጊው ጥናት እና ዲዛይን መዘጋጀቱን፤  በጥናቱ መሰረት በተመረጡ ቦታዎች ወደ ተጨማሪ ስራ የሚገባ መሆኑን ገልጸዋል።

43. በቱሪስት መዳረሻ አካባዎች ለቱሪዝም ኢንቨስትመንት የሚውሉ አካባቢዎች አለመለየታቸው የቱሪስት መዳረሻ ልማት ክፍተት የሚስተዋልባቸውን ስፍራዎች ለማልማት የሚካሄዱ ኢንቨስትመንቶች በጥናት ላይ የተመሰረቱ እንዳይሆኑ በማድረግ ክፍተት ያለባቸው አካባቢዎችን የመዳረሻ ልማት ሽፋን ማዳረስ እንዳይቻል በማድረግ ጎብኝዎች በዘርፉ እርካታ እንዳይሰማቸው በማድረግ፣ የጎብኝዎችን ፍሰት እንዲቀንስ በማድረግ፣ ዘርፉ ሊያስገኝ የሚችለውን የስራ ዕድልና ከውጭ ጎብኝዎችን በመሳብ የተሻለ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታን ከማረጋገጥ አኳያ አሉታዊ አስተዋጽኦ ይኖረዋል።



- በጢያ ዓለም አቀፍ ቅርስ የመብራትና የውሃ አገልግሎቶች አለመኖራቸውን፤



ምስል ቁ. 2፡ በጢያ ዓለም አቀፍ ቅርስ የውሃ አቅርቦት የሌላቸው የመጸዳጃና ሻዎር አገልግሎት መስጫ

- በስንቅሌ ቆርኬዎች መጠለያ ብሔራዊ ፓርክ የመሰረተ ልማት ክፍተቶች እንዲቀረፉ በፌዴራል ዱር እንስሳ ጥበቃ ባለስልጣን በኩል ጥናት የተደረገ ቢሆንም፤ ይሁን እንጂ ጥናቱን መሰረት አድርጎ ክፍተቶችን መሙላት ላይ ችግር መኖሩን፤ እንዲሁም በፓርኩ የቱሪስት ማረፊያ አለመኖሩን፤ የመብራት ችግር መኖሩን፤ ለእንስሳቱም ሆነ ለቱሪስቶች የውሃ አገልግሎት በፓርኩ አለመኖሩንና ከአላባ ከተማ በተሽከርካሪ በማመላለስ የሚጠቀሙ መሆኑን፤ የመጸዳጃ አገልግሎት ግንባታው ያልተጠናቀቀ መሆኑንና የውሃ አገልግሎት የሌለው መሆኑን፤ ለቱሪስቶች መመገቢያ ስፍራ (Picnic Site) አለመኖሩን፤ እንዲሁም በመጠለያ ፓርኩ በየአመቱ የውስጥ ለውስጥ መንገድ የሚጠገን ቢሆንም፣ መሬቱ አስቸጋሪ በመሆኑ በዝናብ ምክንያት የሚበላሽ መሆኑን

በኦዲት ወቅት ከተከለሱ የሰነድ ማስረጃዎች፣ በናሙና ተመርጠው ለታዩ ብሔራዊ ፓርኮችና ቅርሶች ጉዳዮ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ከቀረቡ ቃለ-መጠይቆችና በመስክ ጉብኝት ወቅት ለማወቅ ተችሏል።

44. ጉዳዮን በተመለከተ የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት የስራ ኃላፊዎች በዝርዝር ኦዲት ማጠቃለያ ላይ ተጠይቀው፤ በመዳረሻ ስፍራዎች የመሰረተ ልማት ችግር የመኖሩ ምክንያት ዘርፉ ሰፊ ኢንቨስትመንት የሚጠይቅ መሆኑን ገልጸው፤ ነገር ግን ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የካፒታል በጀት መመደብ የተጀመረው በ2015 በጀት ዓመት መሆኑን ገልጸዋል። በተጨማሪም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሲቋቋም የራሱ የሆነ የቱሪዝም ፈንድ እንዲያቋቁም በአዋጅ ስልጣንና ሀላፊነት ተሰጥቶት የነበረ ቢሆንም ይህ ሳይፈጸም በመቅረቱ በመዳረሻ ስፍራዎች የመሰረተ ልማት ችግሮችን ለመቅረፍ እንዳይቻል የበጀት እጥረት የበኩሉን አሉታዊ አስተዋጽኦ ያደረገ መሆኑን ገልጸዋል።

45. እንዲሁም የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት አስተያየት በዱር እንስሳት ጥብቅ ስፍራዎቻችን/ብ/ፓርኮቻችን ያለውን የመሰረተ-ልማት ክፍተት የመለየትና የተለዩትንም በሂደት መቅረፍ የሚያስችል የጥናት ሰነድና የመሰረተ-ልማት ማስተር ፕላን የኢትዮጵያ ዱር እንስሳት ጥበቃ ባለስልጣን በስሩ ለሚተዳደሩ 11 ብሄራዊ ፓርኮችና ሁለት መጠለያዎች አዘጋጅቶ በትግበራ ላይ የሚገኝ ቢሆንም ይሁንና ያሉትን የመሰረተ ልማት ክፍተቶች ከመቅረፍ አንጻር ተቋሙ ከመንግስት የሚመደብለት በጀት በጥበቃ ቦታዎቹ ካለው መጠነ ሰፊ የመሰረተ ልማት ፍላጎት አንጻር ፈጽሞ የማይጣጣም ከመሆኑ አንጻር በጥበቃ ቦታዎቻችን ያለውን የመሰረተ ልማት ክፍተቶች በከፊል አንኳን ለማሟላት ከፍተኛ ሀብትና የበርካታ አመታትን ልፋትና ጥረት የሚጠይቅ ግዙፍ ተግባር መሆኑ ግንዛቤ ሊወሰድበት እንደሚገባ ገልጸዋል።

46. በቱሪስት መዳረሻ ስፍራዎች መሰረተ ልማት አለመሟላት ብዙ ጎብኚዎች መሳብ እንዳይቻል የሚመጡትም ጎብኝዎችን ምቾት በሚሰጠው አገልግሎት እንዳይረኩ በማድረግ ቆይታቸውን ማራዘም እንዳይቻል የሚያደርግና የቱሪስቶችን ፍሰት በመቀነስ ፓርኮቹ ሊያስገኙ የሚችሉትን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ማግኘት እንዳይቻል የራሱን አሉታዊ አስተዋጽኦ ያደርጋል።

## የቱሪስት መዳረሻ ፕሮጀክቶች አፈፃፀምን በተመለከተ

47. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በነባር የቱሪዝም መዳረሻ ስፍራዎች ላይ እየተካሄዱ ያሉ የመሰረተ ልማት ግንባታ ፕሮጀክቶች ወደ ትግበራ ከገቡ በኋላ በተያዘላቸው የጊዜ ገደብና የጥራት ደረጃ መጠናቀቃቸውን ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል።

48. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ የሰነድ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ-መጠይቆች የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

- በስንቅሌ የቆርኬዎች መጠለያ ብሔራዊ ፓርክ
  - የማሕበረሰብ አቀፍ የእደ ጥበብ ማምረቻ ማዕከል እንዲሁም የመጸዳጃና ሻዎር አገልግሎት ፕሮጀክቶች ግንባታ ለማከናወን በውል ሰጭ ቱሪዝም ሚኒስቴር መ/ቤት እና በውል ተቀባይ ሰናይ ተካ ኮንስትራክሽን ድርጅት በኩል በቀን 24/10/2014 ዓ.ም በ2,980,037.32/ሁለት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሰማንያ ሽህ ሰላሳ ሰባት ብር ከሰላሳ ሁለት ሳንቲም/ የገንዘብ ወጭ በአንድ ወር ውስጥ ለማጠናቀቅ ስምምነት ተደርጎ የነበረ ቢሆንም እስከ ታሕሳስ ወር 2017 ዓ.ም ድረስ (ለሁለት ዓመታት ከአምስት ወራት ያኸል) ያልተጠናቀቀ መሆኑ፤





*ምስል ቁ. 3. በስንቅሌ የቆርኬዎች መጠለያ ብሔራዊ ፓርክ በቀን 24/10/2014 ዓ.ም ተጀምሮ እስከ 09/04/2017 ዓ.ም ያልተጠናቀቀ የሻዎርና መጸዳጃ አገልግሎት መስጫ*


  - በቱሪዝም ሚኒስቴር ክትትል ፒ.ኤች.ኢ. በተሰኘ የዕርዳታ ድርጅት ድጋፍ እየተገነባ ያለው የስንቅሌ ቆርኬዎች መጠለያ ብሔራዊ ፓርክ የማሕበረሰብ አቀፍ ሎጅ የጥራት ጉድለት ያለበት (የተገጠመለት በርና መስኮት ለረዥም ጊዜ አገልግሎት መስጠት የማያስችል/ገና ርክክብ ሳይደረግ የመበስበስ ሁኔታ ማሳየቱ፤ የመስኮት መስታዎቱ የተሰበረ መሆኑ)፤



*ምስል ቁ. 4.፡ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ክትትል እየተገነባ የሚገኘው የስንቅሌ ቆርኬዎች መጠለያ ብሔራዊ ፓርክ የማሕበረሰብ አቀፍ ሎጅ፤*

- በሚኒስቴር መ/ቤቱ የመካከለኛ ዘመን ዕቅድ (ከ2013-2015 ዓ.ም) በአዲስ አበባ ከተማ የሰው ዘር መገኛ ሙዚየም በ1 ቢሊዮን 200 ሚሊዮን ብር በ2013 ተጀምሮ በ2015 ዓመተ ምህረት ለማጠናቀቅ ታቅዶ የነበረ ቢሆንም ለግንባታ የተሰጠውን 4300 ሄክታር ቦታ መረከብ ያልቻለ መሆኑ፣ ከዚህ ጋር በተያያዘ የኢትዮጵያ ቅርስ ጥበቃ ባለስልጣን መ/ቤት ከቦታው ለሚነሱ አካላት ካሳ 9 ሚሊዮን ብር ቢከፈልም ቦታውን መረከብ አለመቻሉንና የሙዚዮሙ ጉዳይ በእንጥልጥል ላይ የሚገኝ መሆኑን፤
- በ2015 ዓመተ ምህረት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሙዚየም ግንባታ በ3 ቢሊዮን ብር በጀት ለመገንባት በዕቅድ ተይዞ የነበረ ቢሆንም እስከ ታሕሳስ ወር 2017 ዓ.ም ድረስ ምንም እንቅስቃሴ አለመደረጉን ከሚኒስቴር መ/ቤቱ የመካከለኛ ዘመን ዕቅድ (ከ2016-2018 ዓ.ም) አፈጻጸም ሪፖርት የተጠቀሰ መሆኑ፤
- በኦሮሚያ ክልል የፕሮጀክቶች ትግበራ መዘግየት ችግር መኖሩን ከክልሉ ቱሪዝም ቢሮ የ2016 ዓ.ም ሁለተኛ ሩብ ዓመት ሪፖርት፤ ታህሳስ 2016 ላይ የተጠቀሰ መሆኑ፤
- በ2014 ዓ.ም በአቢጃታ ሻላ ሐይቆች ብ/ፓርክ የውስጥ ለውስጥ መንገድ ግንባታ ተጀምሮ በዚሁ በ2014 በጀት ዓመት ለማጠናቀቅ ታቅዶ የነበረ ቢሆንም የፕሮጀክት አፈጻጸሙ የተጓተተ መሆኑን ከፓርኩ አፈጻጸም ሪፖርት ላይ የተገለጸ መሆኑን፤
- በሰሜን ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ የሚገኘው የማሕበረሰብ አቀፍ ሎጂ /ኮሚዩኒቲ ሎጅ የጥራት ደረጃውና ዲዛይኑ ደረጃውን ያልጠበቀ መሆኑን፤ እንዲሁም በፓርኩ ውስጥ የሚገኘው ጨነቅ የማሕበረሰብ ሎጂ ጥራቱ ዝቅተኛ መሆኑ ጎብኚዎችን ከንጽሕና ጉድለት ጋር ተያይዞ ለሚከሰት ችግር የሚያጋልጥ መሆኑን ከፓርኩ የልማት ዕቅድ (እ.ኤ.አ 2014) ላይ የተጠቀሰ መሆኑና ችግሩ አሁንም አለመቀረፉን የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች መግለጻቸው፤

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በ2015 በጀት ዓመት ከተመደበለት 401,250,000 ብር/አራት መቶ አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሀምሳ ሽህ ብር/ ካፒታል በጀት 79,357,987.56/ሰባ ዘጠኝ ሚሊዮን ሶስት መቶ ሀምሳ ሰባት ሽህ ዘጠኝ መቶ ሰማንያ ሰባት ብር/ ማለትም 20 በመቶ ብቻ ጥቅም ላይ ማዋል መቻሉ በጀቱን ውጤታማ በሆነ መልኩ በመጠቀም ስራን ከማሳለጥ አንጻር አፈጻጸሙ ዝቅተኛ መሆኑን፣




- በብሔራዊ ፓርኮች በ2016 በጀት ዓመት ተጀምረው በዚሁ በጀት ዓመት ለማጠናቀቅ ታቅደው የነበሩ ፕሮጀክቶች
  - የቦረና ብሔራዊ ፓርክ ጽ/ቤት የኮንስትራክሽን ስራ ጠቅላላ የፊዚካል አፈጻጸሙ 74.9 % መሆኑ፤
  - በገራይሌ እና በማዜ ብሔራዊ ፓርኮች አዲስ የሬንጀር መኖሪያ ቤቶች ለመገንባት ታቅዶ በአማካኝ የሁለቱም ፓርኮች የፊዚካል ስራ አፈፃፀም 52% መሆኑን፤
  - በስንቅሌ ቆርኬዎች መጠለያ ፓርክ ለቆርኬዎች 2 የውሃ መጠጫ ገንዳ ለመገንባት ታቅዶ አፈጻጸሙ 1 (50 በመቶ) መሆኑ፤ እንዲሁም 4 ጠቋሚ ምልክቶች ለማከናዎን ታቅዶ አፈጻጸሙ 2 (50 በመቶ) መሆኑን፤
  - በባቢሌ የዝሆኖች መጠለያ ፓርክ 10 ኪሎ ሜትር ነባር የውስጥ ለውስጥ መንገድን ለመጠገን ታቅዶ አለመከናዎኑ፤
  - ለያንጉዲ ራሳ ብሔራዊ ፓርክ አንድ አዲስ ጽ/ቤት ገንብቶ ለማጠናቀቅ ታቅዶ የነበረ ቢሆንም አለመከናዎኑን የተገለጸ መሆኑ፤ከፓርኮቹ የ2016 በጀት ዓመት አፈጻጸም ሪፖርት ላይ የተጠቀሰ መሆኑን፤

በኦዲት ወቅት ከተከለሱ የሰነድ ማስረጃዎችና በናሙና ተመርጠው ቃለ-መጠይቅ ከቀረበላቸው የብሔራዊ ፓርክ የስራ ኃላፊች ከሰጡት ምላሽ ለመገንዘብ ተችሏል።

49. ጉዳዮን በተመለከተ የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት የስራ ኃላፊዎች በዝርዝር ኦዲት ማጠቃለያ ላይ ተጠይቀው፤ ለፕሮጀክቶች አፈጻጸም መዘግየት ምክንያት በመ/ቤቱ በኩል ፕሮጀክት አስተዳደርን በተመለከተ ያለው ግንዛቤ ዝቅተኛ መሆኑ እንደ ዋነኛ ምክንያት የሚጠቀስ መሆኑን ገልጸው፤ እንዲሁም የስንቅሌ ፕሮጀክት በዕቅድ ተይዞ የተገባበት ባለመሆኑ ወደ ተግባር ሲገባ የበጀት እጥረት በማጋጠሙ፣ ስራውን መደበኛ በሆነ መልኩ የሚከታተል አማካሪ ያልተቀጠረ በመሆኑ ምክንያት የተከሰተ ችግር ነው የሚል ምላሽ ሰጥተዋል።

እንዲሁም የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች የስንቅሌ የቆርኬዎች መጠለያ ፕሮጀክት ግንባታን በተመለከተ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ፤ ፕሮጀክቱ በአንድ ወር እንዲሰራ ስምምነት የተደረሰበት ስራ በስዓቱ መጠናቀቁን፤ ነገር ግን ተጨማሪ ድጋፍ ከአጋር ድርጅቶች በመገኘቱ ከተገነባው ማህበረሰብ-አቀፍ ሎጅ ማእከል ማሻሻያ እንዲደረግ፣ ተጨማሪ የመንገድ፣ አጥር ስራዎች ፒ.ኤች.ኢ /Population, Health and Environment/PHE በተሰኘ ግብረ ሰናይ ድርጅት እና በዱር እንስሳት ጥበቃ ባለስልጣን በኩል ድጋፍ በመገኘቱ፤ እንዲሁም ፓርኩ የሚገኝበት ክልል ከምዕራብ አርሲ ወደ ፓርኩ በቅርብ ርቀት ዉሃ የማስገባት ስራ እተከናወነ በመሆኑ፤ በአካባቢዉ የጸጥታ ችግር የነበረ በመሆኑ ነው። ይሁን እንጅ በአሁኑ ሰዓት ሁሉም ነገር ተጠናቆ እርማት የሚስፈልጋቸዉ ጉዳዮች እርማት ተደርጎባቸዉ ሙሉ በሙሉ ተጠናቆ በአካባቢው ያደራጀናቸው ወጣቶች አስፈላጊው ቁሳቁስ ድጋፍ ተደርጎላቸዉ ለአገልግሎት ዝግጁ የተደረገ ሲሆን በጥር ወር አገልግሎት መስጠት የሚጀምር ይሆናል። በአሁኑ ጊዜ በቆይታ ምክንያት የተስተዋሉ የበርና መስኮት ግድፈቶች በአግባቡ አመራሩ ትኩረት ሰጥቶ እንዲሻሻሉ ማድረጉን ገልጸዋል። የ2015 በጀት አመት የካፒታል ፕሮጀክት አፈጻጸም ዝቅተኛ የሆነው የጅማ አባጅፋር ቤተ መንግስት ለጥገና የተያዘ በጀት ሲሆን ነገር ግን በኮንትራክተሩ እና አማካከሪ  መሃንዲሱ መሰራት የነበራባቸው በወቅቱ ስላልተሰራ ያልተከፈለ ነው ብለዋል።

50. ይሁን እንጂ የስንቅሌ ቆርኬዎች መጠለያ ብሔራዊ ፓርክ የማሕበረሰብ አቀፍ የእደ ጥበብ ማምረቻ ማዕከል፣ የመጸዳጃና ሻዎር አገልግሎት ግንባታ ፕሮጀክትን አለመጠናቀቁን እና የፕሮጀክቱ የግንባታ ውል ከተደረገ ሁለት ዓመታት ከአምስት ወራት በላይ ሳይጠናቀቅ፣ ርክክብም ያልተደረገ መሆኑን የኦዲት ቡድኑ በቦታው ተገኝቶ ያረጋገጠ በመሆኑና በ2015 በጀት አመት ያልተሰራበት የካፒታል በጀት በጣም ከፍተኛ መሆኑ፣ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች በኩል የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል።

51. በመሆኑም ፕሮጀክቶቹ በተያዘላቸው ጊዜና ጥራት አለመጠናቀቃቸው ሲገነቡ ይሰጣሉ ተብሎ የታሰበላቸውን ጥቅም ኅብኝዎች በወቅቱ ማግኘት እንዳይችሉ በማድረግ በመዳረሻ ስፍራዎች ቆይታቸው የሰመረ እንዳይሆንና በመዳረሻ አካባቢዎች ቱሪስቶች ቆይታቸውን ማራዘም እንዳይችሉ፣ ማሕበረሰቡ ከዘርፉ ተጠቃሚ እንዳይሆን የሚያደርግ ከመሆኑም ባሻገር፤ ለፕሮጀክቶቹ በግብዓትነት የሚውሉ የግንባታ ዕቃዎች በጊዜያት ሂደት ለሚከሰት የዋጋ ንረት/Inflation ተጋላጭ እንዲሆኑ በማድረግ ለተጨማሪ የገንዘብ ወጭ እና ለግንባታ መዘግየት ይዳርጋል።

## የፓርክ አስተዳደር ዕቅድ /General Management Plan/ ትግበራን በተመለከተ

52. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለብሄራዊ ፓርኮች አስተዳደር የተዘጋጀው የፓርኮች አስተዳደር እቅድ /General Management Plan/ በታቀደው መልኩ እየተተገበረ መሆኑን ክትትልና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል።

53. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፦

የፓርክ አስተዳደር ዕቅድ (Park Management Plan) የተዘጋጀላቸው ፓርኮች የመሰረተ ልማት ግንባታ ዕቅዱ ባስቀመጠው የትግበራ ወቅት መሰረት እየተከናወነ አለመሆኑን በኦዲት ወቅት በተደረገ የሰነድ ክለሳ እና ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች፣ ለፓርኮችና ቅርስ ጽ/ቤት የስራ ኃላፊዎች ከቀረበ ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል።

54. ጉዳዮን በተመለከተ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት አስተያየት እና በዝርዝር ኦዲት ማጠቃለያ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፤ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች የ10 ዓመት የሥርአት-አያያዝ ዕቅድ /General Management Plan/ በግልጽ እንደተቀመጠው የመሠረተ ልማት አውታሮችን ግንባታን ለማካሄድ በበጀት የተደገፈ እቅድ በሁሉም ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ተዘጋጅቶ ጸድቆ ተግባራዊ እየተደረገ የሚገኝ መሆኑን፤ ነገር ግን በታቀደው አግባብ በጥበቃ ቦታዎቹ መሰረተ ልማቶቹን ማሟላት ያልተቻለው በሥርአት-አያያዝ ዕቅድ ለታቀዱ ተግባራት የተያዘው በጀት እና በመንግስት ለጥገናም ሆነ ለካፒታል ፕሮጀክቶች ለፓርኮቹ የሚመደበው በጀት እጅግ አነስተኛ በመሆኑ ምክንያት ለምሳሌ፡- በ3 ዓመት ውስጥ በስንቅሌ ቆርኬዎች መጠለያ ውስጥ መሰረተ ልማት ለማሟላት የሚያስፈልገው የጥገናና አዲስ ካፒታል ፕሮጀክቶች ወጪ ፍላጎት 33,994,700 ብር ሲሆን በ3 ዓመት ውስጥ ለመጠለያው የተመደበው ጠቅላላ በጀት ከ5,000,000 የማይበልጥ መሆኑን ገልጸዋል።

55. በሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች በቱሪስት መዳረሻ ስፍራ የስርዓት አያያዝ ዕቅድ ላይ የተካተቱ የመሰረተ ልማት ተግባራትን በዕቅዱ መሰረት ለማከናወን የበጀት እጥረት እንደ ምክንያት መጠቀሱ የቱሪዝም ፈንድ እንዲያቋቁም የአስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በሚኒስትሮች ምክር ቤት በወጣው አዋጅ ቁ. 1263/2014 መሰረት ስልጣን የተሰጠው ቢሆንም ፈንዱን አለማቋቋሙ በዘርፉ ያለውን የበጀት ችግር ከማቃለል አኳያ የበኩሉን አሉታዊ አስተዋጽኦ አበርክቷል።

56. ለቱሪስት መዳረሻ ብሔራዊ ፓርኮችና ቅርሶች የተዘጋጀው የፓርኮች አስተዳደር ዕቅድ ትግበራ በዕቅዱ መሰረት እየተከናዎነ አለመሆኑ በመዳረሻ ስፍራዎች መሰረተ ልማት እንዳይሟላ በማድረግ ጎብኝዎች በመዳረሻዎች የሚኖራቸውን ቆይታ የሰመረ እንዳይሆን እና ምቾት እንዳይሰማቸው በማድረግ በስፍራው ቆይታቸውን ማራዘም እንዳይችሉ እንዳይችሉ ያደርጋል።

## በብሔራዊ ፓርኮች የጤና ተቋማት ስለመቋቋማቸው በተመለከተ

57. የቱሪዝም ሚኒስቴር ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመተባበር በብሔራዊ ፓርኮች የቱሪስቶችን ጤንነት ለማስጠበቅ የሚያስችሉ የጤና አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች መቋቋማቸውን ሊያረጋግጥ፣ ተገቢውን አገልግሎት እየሰጡ ስለመሆኑ ሊቆጣጠር፤ እንዲሁም የቱሪስቶች ድንገተኛ አደጋን ለመከላከል የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል።

58. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡

- በቱሪስት መዳረሻ አካባቢዎች የቱሪስቶችን ጤንነት ለማስጠበቅ የሚያስችሉ የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት ያልተቋቋሙ መሆናቸውን፣ የጤና ችግር ሲጋጥም ወደ ህክምና ተቋማት በዝርዝር ኦዲት በናሙና ለተመረጡ ለአብጃታ ሻላ፣ ስንቅሌ የቆርኬዎች መጠለያ፣ አዋሽ፣ ጋምቤላ ገራኢሌ እና ባቢሌ ብሔራዊ ፓርኮች ጉዳዮ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ከቀረበ ቃለ-መጠይቅ እና በኦዲት ወቅት በብሔራዊ ፓርኮች በተደረገ የመስክ ምልከታ እንዲሁም ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ከቀረበ ቃለ-መጠይቅ ለማዎቅ ተችሏል።

59. ጉዳዩን አስመልክቶ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች በኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና በዝርዝር ኦዲት ማጠቃለያ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት ምላሽ፤ ጤና ጣቢያዎችን ማቋቋም የሚኒስቴር መ/ቤቱ ስልጣን ባለመሆኑ ቱሪስቶች በመደራሻ ቦታዎች አቅራቢያ በሚገኙ ጤና ጣቢያ እና ሆስፒታሎች አገልግሎቱን በማግኘት ላይ ይገኛሉ። በተጨማሪም የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በሚኒስቴር መስሪያ ቤታችን

በተዘጋጀዉ የጤና እና ንፅህና ጉዳዮችን ለመከታተል በተዘጋጀ ቸክሊስት መሰረት ቁጥጥር የሚያደርጉ መሆኑን። እንዲሁም በቱሪስቶች ላይ አደጋ ሲደርስ የድንገተኛ አደጋ ችግር ለመፍታት የFIRST AID KIT በመኪናቸዉና በየትኛዉም ጉዞ እንዲይዙና አገልግሎት እንዲያቀርቡ በመደረግ ላይ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

60. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ከላይ የተገለጸውን ምላሽ የሰጡ ቢሆንም፤ ነገር ግን በሚኒስቴር መ/ቤቱ የቱሪዝም ዘርፍ የ10 ዓመት ዕቅድ (እኤ.አ. ከ2013-2022) የቱሪስት መዳረሻ በተለይም ብሔራዊ ፓርኮች ውስጥ የጤና ተቋማትን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ማቋቋም የሚችል ስለሆነ፣ አብዛኛዎቹ ብሔራዊ ፓርኮች ድንገተኛ አደጋ ቢፈጠር በአቅራቢያ ወደ ሌላ ጤና ተቋማት ለማድረስ የተሟላ ግብዓት የሌላቸው በመሆኑ፣ በስራ ኃላፊዎቹ በኩል የተሰጠውን አስተያየት አልተቀበልነውም።

61. በመሆኑም በቱሪስት መዳረሻ አካባቢዎች አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ጤና ጣቢያዎች አለመቋቋማቸው ጎብኝዎች በመዳረሻዎች በሚኖራቸው ቆይታ ከጤና አኳያ ሊያጋጥማቸው የሚችለውን አደጋ መከላከል እንዳይቻል ከማድረጉ በተጨማሪ የጎብኝዎች ፍሰትን በመቀነስ በዘርፉ ያለውን አለም አቀፍ ተወዳዳሪነት ላይ ተጽዕኖ ያደርጋል።

## የቱሪስት መዳረሻ የውስጥ ለውስጥ መንገድ ዝርጋታን በተመለከተ

62. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በብሄራዊ ፓርኮችና ቅርሶች ለጎብኝዎች ምቹ የውስጥ ለውስጥ የተሽከርካሪና የእግረኛ መንገድ መዘርጋቱን የሚያረጋግጥበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል።

- ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡

  በብሔራዊ ፓርኮች የውስጥ ለውስጥ የእግረኛና የተሽከርካሪ መንገድ ችግር መኖሩን፤ ለአብነትም፡-

  - በነጭ ሳር ብሔራዊ ፓርክ ውስጥ የመንገድ ችግር በመኖሩ ምክንያት ስራዎችን ተንቀሳቅሶ ማከናወን ያልተቻለ መሆኑ፤ በመንገዱ አስቸጋሪነት ጎብኚዎች በፓርኩ ነጭ ሳርና የሜዳ አህያ ወደሚገኙበት ሥፍራ ሄደው የዱር እንስሳዎችን ማየት የማይችሉበት ሁኔታ መኖሩ፤

  - በ2015 በጀት ዓመት በነጭ ሳር ብሔራዊ ፓርክ የቱሪስት የእግር መንገድ /foot trail/ ለመስራት ዕቅድ ተይዞ የነበረ ቢሆንም ያልተከናዎነ መሆኑ፤

  - በኦሞ ብሔራዊ ፓርክ የዉስጥ ለዉስጥ መንገድ ችግር ለአጭርና ለረጅም አሰሳ /Patroling/ ስራ ምቹ አለመሆኑን፤

- ○ በቀድሞው የደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ነባርና አዳዲስ ብሔራዊ ፓርኮች ውስጥ በ2015 በጀት አመት 110 ኪ.ሜ የውስጥ ለውስጥ መንገዶች ግንባታ ለማካሄድ ታቅዶ የነበረ ቢሆንም ያልተከናወነ መሆኑን በክልሉ የቱሪዝም ዘርፍ የ2015 በጀት ዓመት የዘጠኝ ወር ዕቅድ ክንዉን ሪፖርት ላይ የተገለጸ መሆኑ፤
- ○ በስንከቅሌ ቆርኬዎች መጠለያ ብሔራዊ ፓርክ በየአመቱ የውስጥ ለውስጥ መንገድ የሚጠገን ቢሆንም፣ መሬቱ አስቸጋሪ በመሆኑ በዝናብ ምክንያት የሚበላሽ መሆኑን ወደ ፓርኩ የሚወስደው የጥርጊያ መንገድ በከባድ ዝናብ ምክንያት ከጥቅም ውጭ መሆኑን፤



*ምስል ቁ. 5፡ ወደ ስንቅሌ የቆርኬዎች መጠለያ የሚወስድ የተሸከርካሪ መንገድ፤*

- በአብጃታ ሻላ ሐይቆች ብሔራዊ ፓርክ ጎብኝዎችን ስርዓት ባለው መልኩ በሁሉም አቅጣጫ ፓርኩን ለመጎብኘት የሚያስችል፤ የውስጥ ለውስጥ የእግረኛና የተሸከርካሪ መንገድ አለመኖሩን አስመልክቶ፤ ከቱሪስቶች እና ከአስጎብኝ ድርጅቶች በኩል መንገድ ለምን እንደማይዘረጋ ጥያቄ የሚቀርብ መሆኑ፤

*ምስል ቁ. 6፡ በአብጃታ ሻላ ሐይቆች ብሔራዊ ፓርክ የሚገኝ የተሸከርካሪና የእግረኛ መንገድ፤*

- በጢያ ትክል ዲንጋይ ከአስፓልቱ ወደ ግቢው የሚያደርስ የጥርጊያ መንገድ ቢኖርም፤ ይሁን እንጂ አስፓልት ወይንም ኮብል ቢነጠፍ የበለጠ ቱሪስት መሳብ ይቻል እንደነበር፤ በስፍራው ያለው የውስጥ ለውስጥ መንገድ ቅርሱ ካለው አለም አቀፋዊ ይዘት አንጻር የማይመጥን መሆኑን

በኦዲቱ ከተከለሱ የሰነድ ማስረጃዎችና ለአብጃታ ሻላ ሐይቆች፣ ስንቅሌ ቆርኬዎች መጠለያ ብሔራዊ ፓርኮች እና ጢያ አለም ዓቀፍ ቅርስ ላይ በተደረገ ምልከታ እንዲሁም ለዱር እንስሳ ጥበቃ ባለስልጣን የስራ ኃላፊዎች ከቀረበ ቃለ መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል።

63. ጉዳዩን በተመለከተ የሚኒስቴር መ/ቤት የስራ ኃላፊዎች በዝርዝር ኦዲት ማጠቃለያ ላይ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በመዳረሻ ስፍራዎች የቱሪስት ተሽከርካሪና የውስጥ ለውስጥ የእግረኛ መንገድ ችግር ለመኖሩ ምክንያት ዘርፉ ሰፊ ኢንቨስትመንት የሚጠይቅ ሲሆን፤ ነገር ግን ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ካፒታል በጀት መመደብ የተጀመረው በ2015 በጀት ዓመት ላይ ነው። በተጨማሪም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሲቋቋም የራሱ የሆነ የቱሪዝም ፈንድ እንዲያቋቁም በአዋጅ ስልጣንና ኃላፊነት ተሰጥቶት የነበረ ቢሆንም ይህ ሳይፈጸም በመቅረቱ በመዳረሻ ስፍራዎች የመሰረተ ልማት ችግሮችን ለመቅረፍ እንዳይችል የበጀት እጥረት የበኩሉን አስተዋጽኦ አድርጓል በማለት ገልጸዋል።

64. በቱሪስት መዳረሻ ስፍራዎ የእግረኛና የተሽከርካሪ መንገዶች አለመሟላት ጎብኝዎች በተመቻቸ ሁኔታ ጉብኝታቸውን ማካሄድ እንዳይችሉ የሚያደርግ ከመሆኑም ባሻገር፤ የመዳረሻ ስፍራዎች የስነ-ምሕዳር ጥበቃ ስራው ላይ ተጽዕኖ የሚያደርግ ሲሆን፤ የቱሪስቶች ቆይታ የሰመረ ከማድረግ አኳያም አሉታዊ ተጽዕኖ ይኖረዋል።

## የቱሪስት አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች ደረጃ ምደባን በተመለከተ

65. ሚኒስቴር/መቤቱ የቱሪስት አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶችን (ሆቴል፣ ፔንሲዮን፣ ሎጅ፣ የባህል ቤቶች) በየጊዜው እየመዘነ ደረጃ ሊሰጥ ይገባል፡፡ ተመዝነው ደረጃ የተሰጣቸውም ደረጃቸውን ጠብቀው እየሰሩ ስለመሆናቸው ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡

66. የሆቴሎችን ደረጃ ለመመደብ የሚረዳ በኢትዮጵያ ደረጃዎች አገልግሎት (የቀድሞው ኤጀንሲ) ስታንደርድ ተዘጋጅቶ ሥራ ላይ ውሏል፡፡ ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት

- የደረጃ ምደባ ስራ በሆቴሎች ብቻ ተግባራዊ የተደረገ መሆኑ፤
- በ2016 በጀት ዓመት ደረጃ የተመደበላቸው የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን 150 ለማድረስ ታቅዶ 64 (42.6 በመቶ) መከናወኑን፤
- በፔንሲዮን፣ ሎጅ፣ ሬስቶራንቶች፣ የባሕል ቤቶች የደረጃ ምደባ ስራ ያልተጀመረ መሆኑ፤
- ሎጅ፣ ሬስቶራንት፣ ፔንሲዮንና የባሕል ቤቶችን ለመመዘን የሚያስችል መመሪያ ያልተዘጋጀ መሆኑ፤
- በአስጎብኝ ድርጅቶች ላይ የብቃት ማረጋገጥ ስራ የማይሰራ መሆኑንና መመሪያም ያልተዘጋጀ መሆኑን፤
- አዳዲስ ተቋማት ስራ ሲጀምሩ በተገቢው ጊዜ ማለትም አገልግሎት መስጠት ከጀመሩ በአንድ ዓመት ጊዜያት ውስጥ እና ከሦስት ዓመታት በኋላ የዳግም ደረጃ ምደባ ስራ የማይከናወን መሆኑ፤
- የቱሪስት አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች የደረጃ ምደባ ስራ በዘመቻ የሚከናወን በመሆኑ ተገንብተው ወደ አገልገግሎት የገቡ አዳዲስ ሆቴሎችን በደረጃ የመመደብ ተግባር እና የዳግም ደረጃ ምደባ ስራ መመሪያው በሚፈቅደው ጊዜያት ውስጥ ሳይከናዎን የቆየ መሆኑ፤
- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በ2011 ዓ.ም የኮከብ ደረጃ ምደባ ከተካሄደ በኋላ 2014 ዓ.ም ላይ የደረጃ ምደባ ሂደቶች የነበሩ ቢሆንም ይፋ የማድረጉ ስራ ዘግይቶ ከሁለት ዓመት በኋላ 2016 ዓ.ም ላይ የተገለጸ መሆኑ ለከተማ አስተዳደሩ የባሕል፣ ስፖርትና ቱሪዝም ቢሮ የስራ ኃላፊዎች ከቀረበ ቃለ-መጠይቅ ለመረዳት የተቻለ መሆኑ፣

በኦዲት ወቅት ከተከለሱ የሰነድ ማስረጃዎችና በናሙና ተመርጠው ለታዩ የክልል የቱሪዝም መስሪያ ቤት የስራ ኃላፊዎች ከቀረበ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

67. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች በኦዲት ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት አስተያየት፤ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የደረጃ ምደባ ስራውን ሲያቅድ  በክልሎችና በአዲስ

አበባ የሚገኙ አዲስ አገልግሎት የጀመሩ ሆቴሎችን በመለየት መሆኑ፣ በ2016 ዓ.ም በተለያዩ የሀገሪቱ ክልሎች የሚገኙ 150 ሆቴሎችን በደረጃ ለመመዘን ያደቀ ቢሆንም ለደረጃ ምዘና ድጋፍ ከተለዩ ሆቴሎች መካከል ለምዘና ብቁ መሆን የቻሉት 62 ብቻ መሆናቸውን፤ በሌላ በኩል አንዳንድ ክልሎች የደረጃ ምዘና ድጋፍ ተደርጎላቸው ለምዘና ዝግጁ የሆኑ ሆቴሎች ቢኖሩም በነበረው የፀጥታ ችግር ምክንያት የምዘና ጊዜያቸው እንዲራዘም ጥያቄ በመቅረቡ በተያዘው ጊዜ ሳይመዘኑ በመቅረታቸው አፈፃፀሙን ዝቅ ያደረገው መሆኑን፤

68. እንዲሁም ከዚህ ቀደም በሆቴሎችና ሪዞርቶች ላይ ብቻ የምዘና ስራ ሲካሄድ የቆየ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት ሎጆችና ሬስቶራንቶችን በደረጃ ለመመዘን የሚስችል ሀገራዊ መመዘኛ መስፈርት ተዘጋጅቶ በረቂቅ ደረጃ የተጠናቀቀ ሲሆን በቀጣይ ህጋዊ ሂደቱን ተከትሎ ለባለድርሻ አካላት ለውይይት ቀርቦ ተግባራዊ ለማድረግ መታቀዱን፤አዳዲስ ሆቴሎች ላይ በተገቢው ጊዜ የደረጃ ምደባ ማካሄድን በተመለከተ ከ2014 በጀት ዓመት ጀምሮ በየዓመቱ በደንቡ በተቀመጠው አግባብ በደረጃ እንዲመደቡ ለማድረግ የታቀደ ቢሆንም አንደኛ ባለሀብቱ በተያዘው ጊዜ ለመመደብ ፈቃደኛ አለመሆን ሁለተኛው በደረጃ ምዘና ድጋፍ ሱፐርቪዥን ወቅት አብዛኞቹ ተቋማት የኮከብ ደረጃ ለመመዘን ብቁ አለመሆን ችግር ማጋጠሙን ገልጸዋል።


69. የደረጃ ምደባ በአገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች (ሆቴል፣ ሎጂ፣ ሬስቶራንት፣ ፔንሲዮን፣ አስጎብኝ ድርጅቶች) ላይ አለመከናዎኑ፤ በዘርፉ የተሰማሩ ባለሀብቶች ያለአግባብ የቀረጥ ነጻ ተጠቃሚ እንዲሆኑ፤ በድርጅቶቹ መካከል ጤናማ የሆነ ውድድር እንዳይኖር በማድረግ ጥራቱን ያልጠበቀ አገልግሎት አቅርቦት እንዲኖር፣ ጎብኝዎች ቆይታቸው ያልሰመረ እንዲሆን በማድረግ ከአገልግሎት አሰጣጥ ጥራት አኳያ የሀገሪቱን የአገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች ገጽታን የሚጎዳ ከመሆኑም ባሻገር በዘርፉ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን የሚጎዳ ሲሆን፤ እንዲሁም የቱሪስት አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶት/ሆቴሎች የደረጃ ምደባ አፈጻጸም ዝቅተኛ መሆን የድርጅቶቹ አገልግሎት አሰጣጥ ጥራት ላይ ችግር ይፈጥራል።

**የደረጃ ምደባ የተደረገላቸው ሆቴሎች ላይ የሚከናወን ክትትልን በተመለከተ**

70. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሆቴሎች ደረጃ ምደባ አሰጣጥ ትክክለኛውን የደረጃ ምደባ መስፈርትን በኋላ ለደረጃቸው የሚያስፈልገውን መስፈርት ጠብቀው አገልግሎት እየሰጡ ስለመሆኑ ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል።

71. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ-መጠይቆች የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

- ሆቴሎች የመመዘኛ መስፈርት በማውጣት የክትትል ሥራ የሚሰራ ቢሆንም በ2016 በተከናወኑ ክትትሎች በናሙና ለኦዲቱ ከቀረቡት የክትትል ቅጾች ላይ በሱፐርቪዥን ባለሙያዎቹ ከተዘጋጀው የመመዘኛ ቅጽ /Check List/ ውስጥ
    - የሆቴሉን ውስጣዊ እና ውጫዊ ገጽታ፣
    - የእንግዳ መቀበያ ክፍል፣
    - የቤት አያያዝ /House Keeping፣
    - ደሕንነትና ጥበቃ፣
    - የሰራተኞች ሙያ ብቃት፣
    - የሰራተኞች አገልግሎት፣
    - የሰራተኞች መብትና ግዴታ ማሳዎቂያ ማቴርያሎች፣
    - የአገልግሎት ጥራትና ቁጥጥር ስርዓት፣
    - የሆቴሉ አጠቃላይ ገጽታና ደረጃን
- ለመገምገም/ ለመመዘን የተዘጋጁት መመዘኛ ቅጾች በሱፐርቪዥን ባለሙያዎቹ ያልተሞሉ መሆናቸው፤ እንዲሁም ቅጹ ላይ ቼክሊስቱን የሞሉት ባለሙያዎች በክትትሉ መሠረት ለድርጅቱ የተሰጠው ደረጃ ባለበት የሚያስቀየው ወይም የሚያሻሽለው ወይም ከደረጃ በታች የሚያወርደው ስለመሆኑ አስተያየት መሙላት ያለባቸው ሥፍራ ላይ ምንም አይነት የማይሞሉ እንዲሁም የሚመለከተው የስራ ክፍል አስተያየት የማይሰጥበትና የማይፈረም መሆኑ በናሙና ከቀረቡ ቅጾች (ቼክሊስቶች) መታወቁ፣ (ከታች ያለውን ሠንጠረዥና አባሪ 4 ይመልከቱ)




- በአገልግሎት ዘርፍ የሚሰማሩ የግል ባህብቶች በወሰዱት የኢንቨስትመንት ኮከብ ደረጃ አገልግሎታቸውን ያለመስጠት ችግር ያለ ሲሆን፤ እንዲሁም አንዳንዶቹ በሚደረግላቸው ድጋፍና ክትትል የማሻሻያ እርምጃ አለመውሰድ ችግር መኖሩ፤

- በቱሪስት አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች ላይ የተጠናከረና ወቅቱን የጠበቀ ሱፐርቪዥን እየተካሄደ አለመሆኑ፤ እንዲሁም አስገዳጅ ቅድመ ሁኔታዎችን ያላሟሉ ተቋማት ላይ የተጠናከረ ክትትል አለመደረጉ፤

- የሆቴሎች የኮከብ ደረጃ ምደባ መመሪያ ቁ. 1/2014 በኮከብ ደረጃ የተመደቡ ሆቴሎች ላይ በአንድ ዓመት ውስጥ 2 ጊዜ ክትትል መደረግ እንዳለበት በግልጽ ያስቀመጠ ቢሆንም፣ ይህ ስርዓት የማይተገበር መሆኑ፤

- አገልግሎት መስጠት ጀምረው በመመሪያ መሰረት የሚመዘኑ ሆቴሎች የአስገዳጅ የእሳት አደጋ መስፈርት አለማሟላታቸው፤ ክፍተቶች በሪፖርት ከተመላከቱ በኋላ ተቋማቱ (ሆቴሎች) የእርምት እርምጃ ስለመውሰዳቸው ክትትል የማይደረግ መሆኑን፤

- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የዕሳትና አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን በሚኒስቴር መ/ቤቱ በቀን 24/12/2016 ዓ.ም ደ.ቁ. ቱሚ/300/367/16 የእሳት አደጋ ደህንነት ብቃት ማረጋገጫ የተሰጣቸውን እና ዓመታዊ እድሳት የተደረገላቸውን ሆቴሎች መረጃ አጣርቶ እንዲያቀርብ የተጠየቀውን ጥያቄ መሰረት አድርጎ ኮሚሽኑ በመስከረም 06/2017 ዓ.ም በሰጠው ምላሽ ከ113 ሆቴሎች ውስጥ 71 የሚሆኑት ሆቴሎች የዕሳት አደጋ መከላከል የምስክር ወረቀት ከነጭራሹ የሌላቸው መሆኑን፤ ዝርዝሩ ውስጥ ከተካተቱት ሆቴሎች ውስጥ 10 የሚሆኑት ዓመታዊ የእሳት አደጋ መከላከል የምስክር ወረቀት ዕድሳት ያላደረጉ መሆኑን፤ ይህም አስገዳጅ የደረጃ ምደባ መስፈርት የሆነውን የዕሳት አደጋ ደህንነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳይኖራቸው በደረጃ የመመደብ ስራ መካሄዱን የሚያረጋግጥ መሆኑ፤


- በሀገር አቀፍ ደረጃ ያለውን የአገልግሎት አሰጣጥ ችግር ከመሰረቱ መቅረፍ አለመቻሉ፣ እንዲሁም ደረጃቸውን የጠበቁ የመኝታ ክፍሎችን ለቱሪስቶች በማቅረብ ረገድ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከ140 ሀገራት ኢትዮጵያ 134ኛ ደረጃ ላይ የምትገኝ መሆኑን ከሚኒስቴሩ የመካከለኛ ዘመን ዕቅድ (ከ2016-2018 ዓ.ም) ላይ መገለጹ፤

- የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሱፐርቪዥን ዴስክ ለቱሪስት አገልግሎቶች ብቃት ማረጋገጥና ደረጃ ምደባ ስራ አስፈጻሚ በቀን 24/05/2016 ዓ.ም ደረጃ በተሰጣቸው የቱሪስት አገልግሎት ሰጭ ሆቴሎች ላይ በአዲስ አበባ ከተማ ባደረገው መደበኛ ሱፐርቪዥን፡-
  - በኢ.ሊ.ሊ. ሆቴል አስገዳጅ ቅድመ ሁኔታዎች ተብለው ከተለዩ መስፈርቶች ውስጥ የእሳት አደጋ ከመከላከል አንጻር ሰርተፍኬት ቢኖርም ያልታደሰ መሆኑን፣ የአካባቢ ጥበቃን ትኩረት ሰጥቶ ከመስራት አኳያ ሰርተፊኬት የሌለው መሆኑን፣

የባህልና ቱሪዝም የብቃት ማረጋገጫው ከ2015 ዓ.ም ወዲህ ያልታደሰ መሆኑን ማረጋገጡ፤

  - በፓስፊክ ሆቴል የእሳት አደጋ ከመከላከል አንጻር፣ ከንጽህና አጠባበቅ አንጻር፣ የአካባቢ ጥበቃን ትኩረት ሰጥቶ ከመስራት አንጻር ሰርትፊኬት የሌለው መሆኑን፣ እንዲሁም የባህልና ቱሪዝም የብቃት ማረጋገጫው ከ2015 ዓ.ም ወዲህ ያልታደሰ መሆኑን፤
  - በራድሰን ብሉ፣ ጎልደን ቱሊፕ እና ኔክሰስ ሆቴሎች የአካባቢ ጥበቃን በተመለከተ ትኩረት ሰጥቶ ከመስራት አንጻር ሰርተፊኬት የሌለው መሆኑን፤
  - ሂልተን ሆቴል የእሳት አደጋ እና የአካባቢ ጥበቃን በተመለከተ ትኩረት ሰጥቶ ከመስራት አንጻር ሰርተፊኬት የሌለው መሆኑን፤ ኪንግ ሆቴል የእሳት አደጋ ከመከላከል፣ ከንጽህና አጠባበቅ እና የአካባቢ ጥበቃን ከመስራት አንጻር ሰርተፊኬት የሌለው መሆኑን ማረጋገጡ፤
  - ሳሬምና ናዝራ ሆቴል የአካባቢ ጥበቃን በተመለከተ ከመስራት አንጻርና የባህልና ቱሪዝም ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት የሌላቸው መሆኑን፤

- በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተዘጋጀው የቱሪስት አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች የኮከብ ደረጃ ምደባ መመሪያ ቁጥር 1/2014 ማንኛውም የቱሪስት አገልግሎት ሰጭ ድርጅት የተመደበበትን ደረጃ መስፈርት ያላሟላ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ጉድለቱን እንዲያስተካክል በሚኒስቴሩ በኩል ከ30 ቀናት ላልበለጠ ጊዜ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ሊሰጥና ድርጅቱ በተሰጠው የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ መሰረት በወቅቱ ያላስተካከለ እንደሆነ የደረጃ ምደባ የምስክር ወረቀቱ እንዲሰረዝና የተሰጠውም አርማ እንዲመለስ ማድረግ እንደሚገባ የሚገልጽ ቢሆንም፤ በግንቦት 2014፣ ሕዳር 2015 እና ሐምሌ 2015 ዓ.ም በሀዋሳ፣ በአዳማ፣ ዱከም፣ ቢሾፍቱ፣ ለገጣፎና ሻሸመኔ ከተሞች በሚገኙ 64 አዳዲስ ሆቴሎች ላይ የደረጃ ምደባ ምዘና በሚኒስቴሩ ተካሂዶ 36 የሚሆኑት ሆቴሎች እስከ ቀን 27/01/2017 ዓ.ም ድረስ አስገዳጅ የእሳት አደጋ የምስክር ወረቀት አሟልተው አለማቅረባቸው፤ ይህም ከተጠቀሰው መመሪያ አንጻር በድርጅቶቹ ላይ የተወሰደው እርምጃ ወደ ሁለት አመት ገደማ የዘገየ መሆኑን የቱሪዝም ሚኒስቴር ለኦሮሚያ ቱሪዝም ኮሚሽን በደ.ቁ. ቱሚ/100/596/17 ቀን 27/1/2017፤ እና ለኢ.ፌዲሪ ጉምሩክ ኮሚሽን በደ.ቁ. ቱሚ/100/596/17፣ ቀን 27/1/17 ዓመተ ምሕረት ከተጻፈ ደብዳቤ ለመረዳት መቻሉ፤




- ከቀረጥ ነጻ ተጠቃሚ የሆኑ ሆቴሎችን እና አስጎብኝ ድርጅቶች ተገቢውን ክትትል በማድረግ መረጃቸው ተደራጅቶ በፌዴራልም ሆነ በክልል ደረጃ አለመያዙ፣
- ከቀረጥ ነጻ እቃዎችን አስገብተው አገልግሎት መስጠት የጀመሩ አዳዲስ ሆቴሎች አገልግሎት ከጀመሩ አመት አልፏቸው በደንብ ቁጥር 173/2002 መሰረት በደረጃ የመመደብ ግዴታ ያለባቸው ቢሆንም በኮከብ ደረጃ ለመመደብና የሱፐርቪዥን ስራ እንዳይከናዎን የሚፈልጉ መሆኑ፤
- በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኩል በቀን 30/01/17/ ደ.ቁ. ቱሚ/100/597/17 ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባሕል፣ ኪነ-ጥበባትና ቱሪዝም ቢሮ በ13 ሆቴሎች ላይ በዘርፉ የተሰጣቸውን የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንዲነጠቁ እና ተጨማሪ አስተዳደራዊ እርምጃ እንዲወሰድ የሚጠይቅ ደብዳቤ የተጻፈ ሲሆን፤ ይህንን በተመለከተ የኦዲት ቡድኑ ደብዳቤው ለተጻፈለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባሕል፣ ኪነ-ጥበባትና ቱሪዝም ቢሮ ጥያቄ አቅርቦ የነበረ ሲሆን፤ ቢሮው በተጠቀሱት ድርጅቶች ላይ እርምጃ የመውሰድ መብት የሌለው መሆኑንና በከተማዋ በኮከብ ደረጃ የሚመደቡ ሆቴሎች የከተማ አስተዳደሩን የባሕል፣ ኪነ-ጥበባትና ቱሪዝም ቢሮ የብቃት ማረጋገጥ የምስክር ወረቀት በየ ዓመቱ ማረጋገጥ የሚገባቸው የነበረ ቢሆንም እስከ 5 ዓመታት ድረስ የቢሮውን የምስክር ወረቀት ያልወሰዱ ሆቴሎች መኖራቸውን ለከተማ አስተዳደሩ የባሕል፣ ስፖርትና ቱሪዝም ቢሮ የስራ ሀላፊዎች መግለጻቸው፤

በኦዲቱ ወቅት ከተከለሰ ሰነዶችና ከቀረቡ መጠይቆች መረዳት ተችሏል።

72. የሚኒስቴሩ የስራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት አስተያየት፤ በኮከብ ደረጃ ለመመደብ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ወስደው ብቁ ያልሆኑ ሆቴሎች ላይ

አስተዳደራዊ እርምጃ እንዲወሰድ ለሚመለከታቸው አካላት የማሳወቅ ስራ መሰራቱን ገልጸው፤ አስገዳጅ የእሳት አደጋ መስፈርትን በተመለከተ በሆቴሎች ላይ ክትትል ማድረጉን፤ አስፈላጊውን የእርምት እርምጃም እንደሚወሰድ፣ ለሚመለከታቸው አካላትም የእርምትት እርምጃ እንዲወስዱን በደብዳቤ የገለጸ መሆኑን፤ እንዲሁም የተጠናከረ የቁጥጥር ስራን በተመለከተ ጥረት የተደረገ ቢሆንም አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ከኮቪድ ጉዳት እያገገሙ ያለ በመሆኑና ሀራዊ ሁኔታም ተፅእኖ ያሳደረበት በመሆኑ ሚንስቴር መ/ቤቱ በአብዛኛው ትኩረት ሰጥቶ ሲያከናውን የነበረው የድጋፍ ስራ መሆኑን ገልጸው፤ መመሪያ ቁ 1/2014ን ጠቅሶ በአገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች ላይ በአንድ ዓመት ውስጥ 2 ጊዜ መደበኛ የክትትልና ቁጥጥር ሥራ ማካሄድን በተመለከተ በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ዘርፉ በኮቪድ በመጎዳቱ ባለፉት ዓመታት በትኩረት ሲሰራ የነበረው የድጋፍ ስራ በመሆኑ ቁጥጥሩ ላይ ሳይሆን አገልግሎት ሰጭ ተቋማትን የማገዝ ሥራ ሲሰራ የነበረ መሆኑን ገልጸዋል።

73. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ይህን ምላሽ ቢሰጡም የእሳት አደጋ መስፈርት አለመሟላትን በተመለከተ ክትትል ይደረጋል፣ አስፈላጊው የእርምት እርምጃም ይወሰዳል ለሚመለከታቸው አካላትም የእርምት እርምጃ እንዲወስዱ በደብዳቤ ተገልጿል፤ በሚል ለተሰጠው አስተያየት የቀረበው የሰነድ ማስረጃ አሰራሩ ከሚጠይቀው ሂደት ውጭ ከ2 ዓመታት በላይ የዘገየ በመሆኑን አስገዳጅ የደረጃ ምደባ መስፈርት የሆነውን የእሳት አደጋ ደህንነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳይኖራቸው በደረጃ የመመደብ ስራ የተካሄደ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም።

74. በመሆኑም አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች አስገዳጅ የደረጃ ምደባ ከተሰጣቸው በኃላ በየደረጃቸው የሚጠበቅባቸውን አገልግሎት እየሰጡ ስለመሆኑ ክትትል ካልተደረገ ተገልጋዮች ላላገኙት አገልግሎት አላስፈላጊ ክፍያ እንዲከፍሉ ከማድረጉም በላይ በዘርፉ ያለውን ሀገራዊ ገጽታ በመጉዳት የጎብኝዎችን ፍሰት እንዲቀንስ ያደርጋል። እንዲሁም ከቀረጥ ነጻ ተጠቃሚ የሆኑ ድርጅቶች መረጃ ተደራጅቶ አለመኖር ማበረታዎቹ ለተባለላቸው ዓላማ መዋላቸው እንዳይረጋገጥና ዘርፉ ለብልሹ አሰራር ተጋላጭ እንዲሆን በር ይከፍታል።

## የሆቴሎች የመጀመሪያ እና የዳግም ደረጃ ምደባን በተመለከተ

75. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የቱሪት አገልግት ለመስጠት ለተቋቋመ ሆቴሎች ድርጅቱ አገልግሎት መስጠት ከጀመረበት በአንድ አመት ጊዜያት ውስጥ የኮከብ ደረጃ ምደባ ሊያካሂድና ከ3 ዓመታት በኋላ የዳግም ደረጃ ምደባ ሊያካሂድ ይገባል።

76. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት

- እንደ ሀገር የቱሪስት አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች የመጀመሪያ የኮከብ ደረጃ ምደባ (ድርጅቶች አገልግሎት መስጠት ከጀመሩበት በ1 ዓመት ጊዜያት ውስጥ በደረጃ መመደብ) በ2007፣ 2011፣ 2014 እና 2016 ባሉት ዓመታት የተካሄደ ቢሆንም፤ በየ3 ዓመቱ የዳግም ደረጃ ምደባ እስከ ታሕሳስ 2017 ዓ.ም ድረስ ያልተደረገ መሆኑን፤
- በጋምቤላ ክልል 2015 በጀት ዓመት በደረጃ የተመደቡ የቱሪስት አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶችን በቁጥር 4 ለማድረግ ታቅዶ አፈጻጸሙ 1 /25%/ ብቻ መሆኑን ከክልሉ የባህል እና ቱሪዝም ቢሮ የቱሪዝም ዘርፍ፣ የ2015 ዓ.ም የ12 ወር ዕቅድ አፈጻጸም፣ ላይ የተገለጸ መሆኑ፤
- በአገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች የደረጃ ምደባ መመሪያ ቁ.1/2014 መሰረት በቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት ዘርፍ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ወስዶ በኮከብ ደረጃ ለመታቀፍ የቀረጥ ነጻ መብት ተጠቃሚ የሆነ ማንኛውም ድርጅት በአንድ አመት ጊዜያት ውስጥ በደረጃ የማስመደብ ግዴታ ያለባቸው ቢሆንም አንዳንድ አዳዲስ ሆቴሎች ከቀረጥ ነጻ እቃዎችን አስገብተው አገልግሎት መስጠት ከጀመሩ አንድ አመት ቢያልፋቸውም በኮከብ ደረጃ ለመመደብና የሱፐርቪሽን ስራ እንዳይከናዎን የሚፈልጉ መሆኑን ከሚኒስቴሩ የቱሪዝም ዘርፍ የ2015 ዓ.ም ዓመታዊ የስራ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ የተገለጸ መሆኑ፤
- በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተዘጋጀው የቱሪስት አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች የኮከብ ደረጃ ምደባ መመሪያ ቁ. 1/2014 በአገልግሎት ሰጪ ድርጅት ዘርፍ በኮከብ ደረጃ ለመመደብ ማመልከቻ ያስገባ ድርጅት ማመልከቻው ተገምግሞ በአንድ ወር ጌዜያት ውስጥ የደረጃ ምደባ ሊደረግለት እንደሚገባ የሚገልጽ ቢሆንም፤ በ2014 ዓ.ም የደረጃ ምደባ የተካሄደላቸው ሆቴሎች ውጤታቸው ሳይገለጽ አንድ ዓመት ማስቆጠሩ፣
- በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልላዊ መንግስት በ2015 ዓ.ም 3 የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን በኮኮብ ደረጃ ለመመደብ ታቅዶ የነበረ ቢሆንም አለመከናዎኑ፤
- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቱሪስት አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች አገልግሎት መስጠት ከጀመሩ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ የደረጃ ምደባ ስራ መከናዎን ያለበት መሆኑን በተመለከተ አፈጻጸሙ ወጥነት የሚጎድለው መሆኑን፤ የዳግም ደረጃ ምደባ ቢሆንም መደበኛ አሰራሩን ጠብቆ የማይካሄድ መሆኑን ለከተማ አስተዳደሩ የባሕል፣ ኪነጥበባትና ቱሪዝም ቢሮ የስራ ኃላፊዎች ከቀረበ መጠይቅ ለመረዳት መቻሉ፤
- በኦሮሚያ ክልል አገልግሎት መስጠት ከጀመሩ በ1 ዓመት ጊዜያት ውስጥ የደረጃ ምደባ ማስመዘን ያለባቸው ቢሆንም ይህ አሰራር እየተተገበረ አለመሆኑን፤ በክልሉ

በ2007 ዓ.ም ላይ ተመዝነው ኮከብ ደረጃ የተሰጣቸው 66 ሆቴሎች ይህ መጠይቅ እስከቀረበበት (05/03/2017 ዓ.ም) ድረስ ዳግም ደረጃ ምደባ አለመከናዎኑን ለክልሉ የባሕልና ቱሪዝም ቢሮ የስራ ኃላፊዎች ከቀረበ መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል።

77. ስለጉዳዮ የሚኒስቴሩ የስራ ኃላፊዎች በኦዲት ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ፤ ዳግም ደረጃ ምዘናን በተመለከተ ሚንስቴር መ/ቤቱ በያዝነው በጀት ዓመት ከሐምሌ 01/2016 ዓ/ም ጀምሮ በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ ሁሉም ሆቴሎች ላይ የተከናወነ ሲሆን ከተመዘኑት 86 ሆቴሎች ውስጥ ከግማሽ በላይ አስገዳጅ የእሳት አደጋ መስፈርት ማሟላት ባለመቻላቸው ከሚመለከተው የአዲስ አበባ አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ጋር በመሆን ክትትልና ድጋፍ እየተደረገላቸው የሚገኝ መሆኑን ገልጸዋል።

78. በባለ ኮከብ ሆቴል ኢንቨስተመንት ዘርፍ ለመሰማራት ፈቃድ ወስደው በተቀመጠው አሰራር መሰረት የኢንቨስተመንት ማበረታቻ የወሰዱ ሆቴሎችን በገቡት ውል መሰረት በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ እንዲመዘኑ ከክልሎች ጋር በመሆን ሆቴሎቹ የመለየት ስራ መሰራቱን፤ የድጋፍ ሱፐርቪዥን ስራ ተሰርቶላቸው እንዲመዘኑ እየተደረገ መሆኑን ገልጸው፤ ነገር ግን ከተመዘኑ በኋላ ደረጃ ውስጥ ያልገቡና አስገዳጅ የእሳት አደጋ ያላሟሉትን ጭምር በገቡት ውልና ባለው አሰራር መሰረት የሚመለከተው አካል ጉምሩክ ኮሚሽን፣ የተጠቀሙትን የቀረጥ ነጻ መብት እንዲመልሱ ወይንም እንዲከፍሉ እንዲደረግ የ28 ሆቴሎች ዝርዝር የተላከ መሆኑን ገልጸዋል።

79. የቱሪስት አገልግሎ ሰጭ ድርጅቶች ላይ መመሪያው በሚያዘው የጊዜ ገደብ መሰረት የመጀመሪያ ደረጃም ሆነ የዳግም ደረጃ ምደባ የማይደረግ ከሆነ ድርጅቶቹ በተሰጣቸው የደረጃ ጥራት ልክ አገልግሎት እየሰጡ ስለመሆናቸው ማረጋገጥ እንዳይቻል በማድረግ ለተገልጋዮች ጥራቱን የጠበቀ አገልግሎት ከማቅረብ አኳያ አሉታዊ ውጤት ሊያስከትል ይችላል።

## ዘመናዊ የቱሪዝም መረጃ ስርዓትን በተመለከተ

80. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለአገር ውስጥና ለውጭ ባለሀብቶች የተሟላ የቱሪዝም መረጃ ለመስጠት የሚያስችል ዘመናዊ የመረጃ ስርዓት ዘርግቶ ተግባራ ሊያደርግ ይገባል።

81. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለመጠይቆች የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ www.visitethiopia.travel የሚል ዌብሳይት ከፍቶ እያስተዋወቀ መሆኑ
- አገሪቷ በቱሪዝም ዘርፍ ያላትን እምቅ የቱሪዝም ሃብቶች እና የኢንቨስትመንት አማራጮች በተመለከተ ለውጭና አገር ውስጥ ባለሀባብቶች መረጃዎችን በበቂ መጠንና ጥራት ተደራሽ ማድረግ አለመቻሉን፤
- በቱሪስት መረጃ ማዕከላት አገልግሎት ያገኙ ተገልጋዮችን ቁጥር 150,000 ለማድረስ ታቅዶ አፈጻጸሙ 105,340 (69.9%) መሆኑን ከሚኒስቴር መ/ቤቱ የ2016 በጀት ዓመት አፈጻጸም ላይ

ከተከለሱ ሰነዶች ለማረጋገጥ ተችሏል።

82. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች በዝርዝር ኦዲት ማጠቃለያ ቃለ-መጠይቅ እና ለተላከላቸው የነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት ምላሽ፤ ለተጠቀሰው ችግር ምክንያቱ እንደ ሀገር በምንሳተፍባቸው አለም አቀፍ መድረኮች የኢንቨስትመንት አማራጮቻችን ለይቶ መሸጥ ላይ ችግር በመኖሩ፤ ለዚሁ ተግባር በአለም ዓቀፍ መድረኮች ላይ ዘርፉን ማዕከል ያደረገ ተሳትፎ ባለመኖሩ፤ ለዘርፉ በጀት የመመደብ ልምዱ የሌለ በመሆኑ ሲሆን፤ የሀገር ውስጥ ባለሀብቱን ለመሳብ መድረኮች በበቂ ሁኔታ አለመመቻቸታቸው ለችግሩ እንደ መንስኤ የሚወሰድ መሆኑን፣ አገሪቷ በቱሪዝም ዘርፍ ያላትን እምቅ የቱሪዝም ሀብቶች እና የኢንቨስትመንት አማራጮች ለውጭና አገር ውስጥ ባለሀብቶች ለማስተዋወቅ ባለፉት ዓመታት በርካታ ስራዎች መሰራታቸውን ገልጸዋል፡ እንዲሁም የ2016 በጀት ዓመት የተገልጋዮች መረጃን በተመለከተ ለ105,340 (93.16%) ተገልጋዮች መረጃ መሰጠቱን ገልጸዋል።

83. አገሪቷ በቱሪዝም ዘርፍ ያላትን እምቅ የቱሪዝም ሃብቶች እና የኢንቨስትመንት አማራጮች በተመለከተ ለውጭና አገር ውስጥ ባለሀባብቶች መረጃዎችን በበቂ መጠንና ጥራት ተደራሽ ማድረግ ካልተቻለ ዘርፉ የአገር ውስጥን እና ውጭ ባለሀብቶችን በመሳብ የጎብኚዎችና የኢንቨስተሮች መጠን በማሳደግ ሊያስገኝ የሚገባውን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም የውጭ ምንዛሬ እንዲሁም የስራ እድል ፈጠራ በሚፈለገው ደረጃ ማግኘት እንዳይቻል ያደርጋል።

## በመዳረሻ ስፍራዎች የሚያስፈልጉ ፋሲሊቲዎች ተለይተው ስለመደራጀታቸው በተመለከተ

84. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በቱሪስት መስህብና መዳረሻ ስፍራዎች የሚያስፈልጉ የቱሪስት ፋሲሊቲ ፍላጎቶችን በአይነት፣ በመጠንና በጥራት ተለይተው እንዲታወቁ በማድረግ በዘመናዊ የመረጃ ስርዓት እንዲደራጁ ሊያደርግ ይገባል።

85. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለመጠይቆች የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

- በቱሪስት መስህብና መዳረሻ ስፍራዎች የሚያስፈልጉ የቱሪስት ፋሲሊቲ ፍላጎቶችን በአይነት፣ በመጠንና በጥራት ተለይተው እንዲታወቁ በማድረግ በዘመናዊ የመረጃ ስርዓት እንዲደራጁ ስለመደረጉ በተመለከተ ሙከራዎች ተደርገው የነበረ ቢሆንም፣ ስራው አለመካሄዱን በሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች የተገለጸ መሆኑ፤
- በ2016 በጀት ዓመት በዱር እንስሳት ጥበቃ ባለስልጣን መ/ቤት የጥበቃ ቦታዎች የመሰረተ ልማት ተደራሽነት ሽፋን መረጃ ማደራጀት፣ መተንተንና ወቅታዊ የማድረግ ስራ አፈፃፀሙ 40% መሆኑ፤
- በአብጃታ ሻላ ሐይቆች ብሔራዊ ፓርክ በፓርኩ የሚያስፈልጉ የመሰረተ ልማቶችና አገልግሎቶችን በተመለከተ በጋራ ከዱር እንስሳት ጥበቃ ባለስልጣን መ/ቤት ጋር በ2016 ዓ.ም የመለየት ስራ የተሰራ ቢሆንም፤ ይሁን እንጅ በዘመናዊ የመረጃ ስርዓት ስለመደራጀታቸው መረጃው የሌላቸው መሆኑን በመስክ ኦዲት ወቅት ለፓርኩ ጽ/ቤት የስራ ኃላፊዎች ከቀረበ ቃለ-መጠይቅ ለመረዳት የተቻለ መሆኑ፤
- በስንቅሌ ቆርኬዎች መጠለያ ብሔራዊ ፓርክ የመሰረተ ልማት ክፍተቶች በዱር እንስሳት ጥበቃ ባለስልጣን መ/ቤት በኩል በጥናት የተለየ ቢሆንም በዘመናዊ የመረጃ ስርዓት የማደራቸት ተግባር አለመከናዎኑን ለፓርኩ ጽ/ቤት የስራ ኃላፊዎች ከቀረበ ቃለ-መጠይቅ ለመረዳት መቻሉ፤
- በኦሮሚያ ክልል የመዳረሻ ልማት ክፍተት የመለየት ስራ እንደ ክልል በ2016 በጀት ዓመት ታቅዶ የነበረ ቢሆንም የሚመለከታቸውን አካላት ለማሳተፍ የጊዜ ዕጥረት የነበረ በመሆኑ ያልተከናዎነ መሆኑን፤ እንደ ሚኒስቴር መ/ቤትም በዘርፉ የተሰራ ስራ አለመኖሩን፤ በመዳረሻ ስፍራዎች የሚያስፈልጉ ፋሲሊቲዎችን በዓይነት፣ መጠንና ጥራት ያልተለዩ፤ እንዲሁም በዘመናዊ የመረጃ ስርዓት ያልተደራጁ መሆኑን ለክልሉ የባሕልና ቱሪዝም ቢሮ የስራ ኃላፊዎች ጉዳዩን አስመልክቶ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ከሰጡት ምላሽ ለመገንዘብ ተችሏል።

86. ጉዳዩን በተመለከተ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች በኦዲት ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት አስተያየት፤ በሀገር አቀፍ ደረጃ ያሉ የቱሪዝም መዳረሻ ቦታዎች የቱሪስት ፋሲሊቲ ፍላጎቶቶችና ክፍተቶችን የመለየት  ስራ በተለያየ ጊዜ በተከናወኑ ጥናቶች አማካኝነት በስፋት የተከናወነ እና በዚሁ መሰረት የተለያዩ አዳዲስ መዳረሻዎችን የማልማትና ነባሮቹ ላይ እሴት የመጨመር ስራ ሲከናወን የቆየ መሆኑን ገልጸው፤ ሆኖም ግን  የዘርፉን አጠቃላይ የልማት ስራን ጨምሮ በሀገር አቀፍ ደረጃ በወጥነት አሰናድቶ ደረጃ በደረጃ ተግባራዊ ለማድረግ እንዲረዳ ሀገር አቀፍ የቱሪዝም ሀብት ልየታ (national tourism resource mapping) ስራ በሲዳማ ክልል የተጀመረ ሲሆን

በሁሉም ክልሎች ተሰርቶ በሚጠናቀቅበት ጊዜ ጉዳዮ በዘላቂነት ምላሽ የሚያገኝ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

87. እንዲሁም የስንቅሌ ቆርኬዎች መጠለያ ብሔራዊ ፓርክን በተመለከተ ለተጠቀሰው ነጥብ መስሕቡን ለማስተዋወቅ የመረጃ መስጫ ፕላትፎርም ተዘጋጅቶ ቀጣይ ስራዎችን ለማከናዎን እተሰራ መሆኑን፤ አቢጃታ ሻላ ብሔራዊ ፓርክን በተመለከተ በኦዲቱ የተጠቀሰውን ነጥብ በፓርኩ በቀጣይ የመሰረተ ልማት ክፍተቶችን ለማሟላት በሚደረገዉ ጥረት ዉስጥ ታሳቢ ይደረጋል የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

88. በቱሪስት መዳረሻ ስፍራዎች የመሰረተ ልማት ክፍተቶች ተለይተው በዘመናዊ የመረጃ ስርዓት እንዲደራጁ የማይደረግ ከሆነ ስፍራዎቹ ከመሰረተ ልማት አኳያ ያሉባቸውን ክፍተቶች በተጠና መልኩ በመለየት የማሟላት ሂደቱ ላይ ተግዳሮት የሚፈጥር ከመሆኑም ባሻገር በመዳረሻ ስፍራዎች የመሰረተ ልማት ግንባታ ፍትሃዊ ስርጭት እንዳይኖረው ያደርጋል፡፡

## በመዳረሻዎች የቱሪስት እርካታ ደረጃ መመዘኛ ሥርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ

89. ሚኒስቴሩ የኮከብ ደረጃ በተሰጣቸው ሆቴሎች ላይ የቱሪስቶችን እርካታ ደረጃ ለመመዘን የሚያስችል ወቅታዊ ጥናቶችን የሚከናወኑበትና መረጃቸው የሚጠናቀርበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

90. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ የሰነድ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ-መጠይቆች የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

- በቱሪስት አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች የተገልጋይ እርካታ ግብረ መልስ ስርዓት አለመዘርጋቱ፤
- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሚገኙ የቱሪስት አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች ላይ የቱሪስት እርካታ ደረጃ ለማዎቅ የሚያስችል ስራ አለመሰራቱን ለከተማ አስተዳደሩ ባሕል፣ ኪነጥበባትና ቱሪዝም ቢሮ የስራ ኃላፊዎች ከቀረበ ቃለ-መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡

91. ጉዳዮን በተመለከተ የሚኒስቴሩ የስራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት አስተያየት፤ የኢንፎርሜሽን አገልግሎት/ኢ. ሰርቪስ የሚሰጡ የሚንስቴር መ/ቤቱ አገልግሎት ላይ የግብረ መልስ አሰጣጥ ስርአት የተተገበረ ቢሆንም አጠቃላይ የዘርፉን የሚመለከቱ ጉዳዮችን በተመለከተ የግብረ መልስ ስርዓት ለመዘርጋት ከኢንሳ ጋር

ከሁለት ዓመት በፊት በተጀመረው የቪዚት ኢትዮጵያ ድህረ ገጽ ላይ ምላሽ እንዲያገኝ እየተሰራበት የሚገኝ ሲሆን በአጭር ጊዜ ውስጥ ተጠናቆ ወደስራ እንደሚገባ ይጠበቃል የሚል ምላሽ ሰጥተዋል።

92. በቱሪስት አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች የተገልጋዮች እርካታ ግብረ-መልስ ስርዓት አለመኖር በአግልግሎት አሰጣጥ ዘርፍ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመቅረፍ ከተገልጋዮች የሚሰጡ ግብረ-መልሶችን እንደ ግብዓት በመውሰድ በዘርፉ የአገልግሎት ጥራት የማሻሻል እድልን ይነፍጋል።

## ዘመናዊ የቱሪዝም መዳረሻ ስርዓትን በተመለከተ

93. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ዘመናዊ የቱሪዝም መዳረሻ መረጃ ስርዓት (Tourism Destination Management Information System) ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል።

94. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት የቱሪዝም መዳረሻ አስተዳደር መረጃ ስርዓት /Tourism Destination Management Information System/ ያልተዘረጋ መሆኑን ለሚኒስቴሩ የስራ ኃላፊዎች ከቀረበ ቃለ-መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል።

95. ጉዳዮን በተመለከተ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች በዝርዝር ኦዲት ማጠቃለያና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት ምላሽ፤ የቱሪስት መዳረሻዎች አስተዳደር መረጃ ሥርዓት (የDestination Management Information System) ተግባራዊ ያልሆነበት ምክንያት በቅድሚያ የሀገሪቱን የቱሪዝም ሀብት እና የለሙ መዳረሻ ስፍራዎችን መለየት የሚያስፈልግ በመሆኑ፣ ከዚህ ቀደም በማስተርካርድ ፋውንዴሽን በኩል የDestination Management Information System/ዘመናዊ የመዳረሻ ስርአት አስተዳደር ስርአት ለመዘርጋት የሚያስችል የመጀመርያ ደረጃ ስራ የተጀመረ ሲሆን ነገር ግን የተጀመረው ፕሮጀክት ስራው የጥራት ችግር የተገኘበት በመሆኑ በአዲስ መልክ በሚኒስቴር መስሪቤታችን እና በአጋር ድርጅቶች ለምሳሌ፡- ከኢንሳ ጋር በመተባበር ተሰርቶ በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል የሚል ምላሽ ሰጥተዋል።

96. የቱሪዝም መዳረሻ አስተዳደር ስርዓት/Tourism Destination Management System ባለመዘርጋቱ በሀገሪቱ የሚገኙ የቱሪዝም መዳረሻ ስፍራዎችን በአንድ ቋት ውስጥ በማግኘ ስለ መዳረሻዎቹ አስፈላጊውን መረጃ ማግኘት እንዳይቻል ያደርጋል።

## ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ስትራቴጂካዊ ግንኙነትና ቅንጅታዊ አሠራር መመስረቱን በተመለከተ፣

97. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በቱሪስት መዳረሻ ቦታዎች የመሰረተ ልማት ውስንነቶችን በቅንጅት እንዲቀረፍ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ስትራቴጂካዊ ግንኙነት መስርቶ ሊሰራ ይገባል።

98. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ የሰነድ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ-መጠይቆች የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፦

- በቱሪዝም ኢንቨስትመንት ዘርፍ ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር ያለው ቅንጅት ደካማ መሆኑን በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኩል ከተካሄደ የቱሪዝም ኢንቨስትመንት ክፍተት ጥናት (2016 ዓ.ም) ላይ /Ethiopian Tourisim Investment Gap Analysis 2024/ የተገለጸ መሆኑ፤
- የቱሪዝም ልማት የበርካታ አካላትን አምዳዊና የጎንዮሽ ትስስርና ጠንካራ ቅንጅትን የሚፈልግ እንደመሆኑ በሴክተሩ ባለድርሻዎች መካከል ያለው ትስስር የጠነከረ አለመሆኑን ከሚኒስቴር መ/ቤቱ የ2016 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ላይ የተጠቀሰ መሆኑ፤

99. እንዲሁም ጉዳዮን በተመለከተ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች በኦዲት ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት አስተያየት ከንግድ ሚንስቴር እና ከኢንቨስትመንት ኮሚሽን ጋር ያለውን ችግር ሚኒስቴር መ/ቤታችን ቀድሞ የለየው ሲሆን ችግሩን በዘላቂነት ሊፈታ በሚችል መልኩ በተቋሞች መካከል ግንኙነትና አብሮ መስራት ከዚህ ቀደም የነበረውና የተቋረጠውን አሰራር በተሻለ ሁኔታ ለመዘርጋት ሂደቶች ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ ገልጸው፤ በሴክተሩ ባለድርሻ አካላት መካከል ያለው ትስስር የጠነከረ አለመሆኑ በሚል በኦዲቱ በክፍተት ለተጠቀሰው ነጥብ ችግሩን በአሁኑ ሰዓት ሙሉ በሙሉ መቅረፍ መቻሉን፤ በወቅቱ የነበሩ ችግሮች አሁን የሉም ይበልጥ ለማጠናከር ስራዎች በመሰራት ላይ መሆናቸውን ገልጸዋል።

100. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ይህን ምላሽ ቢሰጡም ለሰጡት ምላሽ ማስረጃ ባለመቅረቡ እና ከተጠቀሱት ባለድርሻ አካላት ጋር መደበኛ የሆነ የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ እየሰራ የሚገኝ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ የሰነድ ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል።

101. በመሆኑም በቱሪስት መዳረሻ ስፍራዎች የመሰረተ ልማት ክፍተቶችን ለመቅረፍ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ስትራቴጂክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የተጠናከረ ቅንጅት

አለመኖር ሚኒስቴር መ/ቤቱ በዘርፉ የሚያከናውቸን ተግባራት ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመተግበር እንዳይቻል ያደርጋል።

## ከክልልና ከፌዴራል የቱሪዝም አካላት ጋር በጋራ ለመስራት የሚያስችል ማዕቀፍ ስለመዘጋጀቱ

102. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክልልና ከፌዴራል የቱሪዝም አካላት ጋር በጋራ የሚሰራበትን ማዕቀፍ በማዘጋጀት በስራ ላይ ሊያውል ይገባል።

103. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለመጠይቆች የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

- በቱሪስት አገልግሎት ዘርፍ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ማለትም (ጉምሩክ ኮሚሽን፣ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን፣ እሳት አደጋ ስራ አመራር...) ቅንጅታዊ የአሰራር ስርዓት ያልተዘረጋ መሆኑን፣ ከቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ብቃት ማረጋገጥና ደረጃ ምደባ ስራ ክፍል የ3 ዓመት አፈጻጸም ሪፖርት (2016 ዓ.ም) ላይ የተጠቀሰ መሆኑ፤
- የቱሪስት አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች ከቀረጥ ነጻ ማበረታቻዎች ለታለመላቸው አላማ ስለመዋላቸው የሚያረጋግጥ ስርዓትና ተቋማዊ ቅንጅት ደካማ መሆኑን ከቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በቃት ማረጋገጥና ደረጃ ምደባ ስራ ክፍል የ3 ዓመት አፈጻጸም አጭር ሪፖርት (2016 ዓ.ም) ላይ የተገለጸ መሆኑ፤
- ከንግድ ሚኒስቴር ጋር የነበረው የስራ ቅንጅት ማለትም (የብቃት ማረጋገጥ ስርዓትና ንግድ ፈቃድ አሰጣጥ፣ እድሳት) ችግር የገጠመው መሆኑን ከቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ብቃት ማረጋገጥና ደረጃ ምደባ ስራ ክፍል የ3 ዓመት አፈጻጸም አጭር ሪፖርት፣ (2016 ዓ.ም) ላይ የተጠቀሰ መሆኑ፤
- ከክልል ቱሪዝም ቢሮዎች ጋር ያለውን ቅንጅት በተመለከተ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለክልሎች ቅርብ ሆኖ የቱሪዝም ሀብታቸውን መጠቀም እንዲችሉ ማድረግ ያለበት መሆኑንና፣ በክልልና በሚኒስቴር መ/ቤቱ መካከል መዋቅሩን ጠብቆ ተቀናጅቶ ከመስራት አኳያ ችግር መኖሩን፤ በክልሎች መካከል ወጥ የሆነ የቱሪዝም አደረጃጀት አለመኖሩ እንደ ሀገር መናበብ እንዳይቻል እያደረገ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለሚኒስቴሩ የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ከቀረበ መጠይቅ ለመረዳት መቻሉ፤
- ለደረጃ ምደባ አስገዳጅ ቅድመ ሁኔታዎችን ከሚያረጋግጡ አካላት ጋር ያለው የስራ ትስስር ጠንካራ አለመሆኑን ፤
- የጢያ አለም አቀፍ ቅርስ ከቱሪዝም ሚኒስቴር እና ከቅርስ ጥበቃ ባለስልጣን ጋር ያለው ግንኙነት የላላ መሆኑን፤ ከ2014 ወዲህ የተደረገ ድጋፍና ክትትል

አለመኖሩን፤ ሪፖርት በጋራ የመገምገምና የማቀድ ተግባር አለመኖሩን፤ ቅርሱ አለም ዓቀፍ ይሁን እንጂ በሀገር አቀፍ ደረጃ ትኩረት የተነፈገው መሆኑን የሶዶ ወረዳ ባሕልና ቱሪዝም ጽ/ቤት የስራ ኃላፊዎች መግለጻቸው፤

- የአዲስ አበበባ ከተማ አስተዳደር ባሕል ኪነጥበባትና ቱሪዝ ቢሮ ከቱሪዝም ሚኒስቴር መ/ቤት ጋር በጋራ የሚሰሩበት ማዕቀፍ አለመኖሩን፤ የዕቅድ ትስስርና ግምገማ ስራም የማይካሄድ መሆኑን፤ ሚኒስቴሩ የደረጃ ምደባ በሚያካሂድበት ወቅት ከከተማ አስተዳደሩ በኩል ባለሙያዎች በታዛቢነት ሊሳተፉ ይገባ እንደነበርና ተሳትፎ የሌላቸው መሆኑን በኦዲት ወቅት ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ከሰጡት ምላሽ ለመረዳት መቻሉ፤
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ባሕልና ቱሪዝም ቢሮ ጋር በዕቅድ ትስስርና ግምገማ ረገድ ቅንጅቱ የላላ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለክልሉ የስራ ኃላፊዎች ከቀረበ ቃለ መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል።

104. ስለጉዳዮ የሚኒስቴሩ የስራ ኃላፊዎች በኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት አስተያየት ከጉምሩክ ኮሚሽን፣ ትራንስፖርት ባለስልጣን እና ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ጋር የቅንጅት አስፈላጊነት በሚኒስቴሩ የተለየ በመሆኑ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ለመቀናጀት እየተሰራበት ያለ መሆኑን ገልጸው፤ ክልሎችን በተመለከተ ለተነሳው ነጥብ የሚኒስቴር መሥሪያቤቱ በአዲስ ከተቋቋመ በኃላ በ2014 ዓ.ም አደረጃጀት በመስራትና ተቋሙን እንደገና በማደራጀት ያሳለፈ በመሆኑ በቀጣይ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱን የሰው ኃይል በማሟላት ወደ ሥራ ሲገባ ከክልል የቱሪዝም ቢሮወች ጋር ሊኖረው ስለሚገባ ግንኙነትና አብሮ ለመስራት ጥረት የሚደረግ መሆኑን ገልጸዋል።
እንዲሁም ከእሳትና ድንገተኛ አደጋዎች ጋር የሆቴሎችን ደረጃ ምደባ ወቅት መሟላት ስለሚገባቸው መስፈሮች አብሮ እየተሰራ ሲሆን በቀጣይ ሥራውን ለማጠናከር የጋራ ውይይት ለማድረግ ፕሮግራም መያዙን ገልጸዋል።

105. በቱሪስት መዳረሻ ስፍራዎች የመሰረተ ልማት ክፍተቶችን ለመቅረፍ ከሚመለከታቸው የክልልና የፌዴራል የቱሪዝም ዘርፍ አካላት ጋር ስትራቴጂክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የተጠናከረ ቅንጅት አለመኖር ሚኒስቴሩ በዘርፉ የሚያከናውቸን ተግባራት ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመተግበር እንዳይቻል ያደርጋል።

## የቱሪዝም ቦርድ ስለመቋቋሙ በተመለከተ

106. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ቱሪዝም ልማት ዘርፍ የሚመለከታቸውን የግል፣ የፌዴራል እና የክልል መንግስት ተቋማትን ለማስተባበር የኢትዮጵያ ቱሪዝም ቦርድ በሕግ እንዲደራጅ ሊያደርግ ይገባል።

107. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለመጠይቆች የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅ ቁ. 1263/2013 መሰረት የግሉ ዘርፍ አካላትንና የቱሪዝም ልማት የሚመለከታቸው የፌዴራል እና የክልል መንግስት ተቋማትን ለማስተባበር የኢትዮጵያ ቱሪዝም ቦርድ እንዲያቋቁም ስልጣንና ኃለፊነት የተሰጠው ቢሆንም ቦርዱ አለመቋቋሙን በኦዲት ወቅት ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ከቀረበ ቃለ-መጠይቅ ለማረጋገጥ ተችሏል።

108. ጉዳዮን በተመለከተ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች በኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ እና በዝርዝር ኦዲት ማጠቃለያ ቃለ-መጠይቅ በሰጡት ምላሽ፤ የቦርድ ማቋቋሚያ መመሪያ ተዘጋጅቷል። የቦርዱ አባላት ሊሆኑ የሚገቡ ተቋማት ተለይተው ቦርዱን ለማቋቋም መመሪያ ተዘጋጅቷል። ተቋቁሞ ወደ ስራ ያልገባበት ምክንያት ለማቋቋም በሂደት ላይ በመሆኑ ነው የሚል ምላሽ ሰጥተዋል።

109. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የቱሪዝም ቦርድን አቋቁሞ ወደ ስራ እንዲገባ አለማድረጉ የሚኒስቴሩን ስትራቴጅክ ግቦች በአግባቡ ለመፈጸም ከሚመለከታቸው የመንግስትና የግል የዘርፉ አካላት በኩል አጋዥ ሀይል እንዳይኖረው በማድረግ ውጤታማ አፈጻጸም እንዳይኖረው ያደርገዋል።

## ክፍል ሦስት

## መደምደሚያ/Conclusion

110. የቱሪስት መዳረሻዎች ልማት እና የአገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች የደረጃ ምደባ አፈጻጸምን ዙሪያ የተስተዋሉ የአሠራር ክፍተቶችን መሰረት በማድረግ የሚከተሉት መደምደሚያ ሃሳቦች ላይ ተደርሷል፡-

- በብሔራዊ ፓርኮችና ቅርሶች ላይ ያሉ የመሰረተ ልማት ክፍተቶችን በሂደት ለመቅረፍ ታሳቢ ተደርጎ መሰረተ ልማትን በንዑስነት ያቀፈ የ10 ዓመት ማኔጅመንት ፕላን በቅርስ ጥበቃ እና ዱር እንስሳ ጥበቃ ባለስልጣናት ከመዘጋጀቱ ውጭ ሌላ የመሰረተ ልማት ግንባታ ማዕቀፍ እንዲዘጋጅ አልተደረገም፣
- በቱሪዝም ኢንቨስትመንት ዘርፍ የሚስተዋሉ የአሰራር ማነቆዎችን የመለየት ስራ በጥር 2016 ዓ.ም የተከናዎነ ቢሆንም በጥናቱ ላይ የተለዩ የአሰራር ማነቆዎች እንዲስተካከሉ አልተደረጉም፣
- የቱሪስት መስህብ ልማት ስታንዳርድ አለመዘጋጀቱን ይህም በመሆኑ እንደሀገር ወጥነት ያለው የመዳረሻ ልማት ስራ ማከናዎን እንዳይቻል የሚያደርግ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለመገንዘብ ተችሏል።
- ለብሔራዊ ፓርኮች ሊያሟሉ የሚገባውን መሰረተ ልማትና አገልግሎት የሚገልጽ ወጥነት ባለው መልኩ ሊተገበር የሚችል ስታንዳርድ ቢዘጋጅም ስለመጽደቁ ማስረጃ አልቀረበም፣
- ፓርኮች ብሔራዊ ፓርክ ለመባል ሊያሟሉ የሚገባውን መስፈርቶች፣ የመሰረተ ልማትና መስጠት ያለባቸው አገልግሎትን የሚገልጽ ስታንዳርድ አልተዘጋጀም፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከ2014 እስከ 2018 ዓ.ም የሚተገበር የቱሪዝም ኢንቨስትመንት እና መሰረተ ልማት ስትራቴጂ በ2014 ዓ.ም ያዘጋጀ ቢሆንም ጸድቆ ወደ ተግባር እንዲገባ አለመደረጉ፤
- በቱሪስት መዳረሻ ስፍራዎ የመሰረተ ልማት አለመሟላት ችግር መኖሩ፣
- የቱሪዝም መዳረሻ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው የጊዜ ገደብና ጥራት መሰረት የማይካሄዱ መሆናቸው፣ በአዲስ አበባ ለመገንባት የታቀደው የሰው ዘር መገኛ ፕሮጀክት ካሣ ከተከፈለ በኋላ ሥራ አለመጀመሩ፣ የብሔራዊ ሙዚየም ግንባታ ከ2015 ጀምሮ ቢታቀድም አልተጀመረም፣ የ2015 በጀት ዓመት የካፒታል በጀት አፈጻጸም ዝቅተኛ ነው፣፡
- በቱሪስት መዳረሻ ብሔራዊ ፓርኮችና ቅርሶች አስተዳደር ዕቅድ/ጀነራል ማኔጅመንት ፕላን ያላቸው በዕቅዱ መሰረት እየተገበሩ አይደለም፣

- እንዲሁም የፓርክ አስተዳደር ዕቅድ /General management Plan/ ያልተዘጋጀላቸው ፓርኮች መኖራቸውን፤
- በቱሪስት መዳረሻ ብሔራዊ ፓርኮች ለጎብኝዎች አገልግሎት መስጠት የሚችሉ የጤና ተቋማት አለመቋቋማቸው፣
- በቱሪስት መዳረሻ ስፍራዎች የውስጥ ለውስጥ የእግረኛና የተሽከርካሪ መንገዶች ችግር መኖሩን በኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል።
- ከቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ውስጥ ደረጃ ምሰፈርት የተዘጋጀውና የደረጃ ምደባ ስራ የተከናወነው በሆቴሎች ላይ ብቻ መሆኑንና
- ለሌሎች የቱሪስት አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች (ሎጂ፣ ሬስቶራንት ‹ፔንሲዮን) ላይ የመመዘኛ መስፈርት ያልተዘጋጀ በመሆኑ ምዘናና ደረጃ መስጠት አለመጀመሩን፤
- አዳዲስ ሆቴሎች ስራ ሲጀምሩና የቀረጥ ነጻ መብት ተጠቃሚ ከሆኑ ከአንድ አመት በኋላ ተመዝነው ደረጃ ሊሰጣቸው ቢገባም የደረጃ ምደባ ስራ የማይከናወን መሆኑን፤
- የ2016 በጀት ዓመት የሆቴሎች ደረጃ ምደባ አፈጻጸም ዝቅተኛ (42 በመቶ) መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል።
- አስገዳጅ የደረጃ ምደባ መስፈርቶችን ሳያሟሉ የደረጃ ምደባ የተካሄደላቸው ሆቴሎች መኖራቸው፣
- ደረጃ በተሰጣቸው ሆቴሎች ላይ የተጠናከረና ወቅቱን የጠበቀ ሱፐርቪዥን እየተካሄደ አለመሆኑ፣ ለክትትል ተብሎ የተዘጋጀው ቅጽ ላይ የተጠቀሱት መስፈርቶች መካከል በጥቂቱ ብቻ ሆቴሎች እየተገመገሙ መሆኑ፣
- የመጀመሪያ ጊዜ ምደባና የዳግም ደረጃ ምደባ መመሪያው በሚያዘው የጊዜ ገደብ ውስጥ እየተከናወነ አይደለም፣
- የደረጃ ምደባ የተካሄደላቸው ሆቴሎች ውጤታቸው ሳይገለጽ አንድ እስከ ዓመት የሚቆይበት ሁኔታ መኖሩን፣።
- በቱሪዝም ዘርፍ የቱሪዝም ሃብቶች እና የኢንቨስትመንት አማራጮችን በተመለከተ ለውጭና አገር ውስጥ ባለሀባብቶች መረጃዎችን በበቂ መጠንና ጥራት ተደራሽ አለማድረጉ፣
- በቱሪስት መዳረሻ ስፍራዎች የሚስተዋሉ የመሰረተ ልማት ክፍተቶች ተለይተው በዘመናዊ የመረጃ ስርዓት ያልተደራጁ መሆናቸው፣፡
- ሚኒስቴሩ በቱሪስት አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች ላይ የተገልጋይ እርካታ ግብረ መልስ ስርዓት አለመተግበሩ፣ረጋገጥ ተችሏል።
- የቱሪዝም መዳረሻ አስተዳደር ስርዓት/Tourism Destination Management System ተግባራዊ አልሆነም።

- የቱሪዝም ልማት የበርካታ አካላትን አምዳዊና የጎንዮሽ ትስስርና ጠንካራ ቅንጅትን የሚፈልግ እንደመሆኑ በሴክተሩ ባለድርሻዎች መካከል ያለው ትስስር የጠነከረ አለመሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል።
- እንዲሁም በቱሪዝም ልማት ዘርፍ የሚመለከታቸውን የግል፣ የፌዴራል እና የክልል መንግስት ተቋማትን ለማስተባበር የሚያስችለውን የኢትዮጵያ የቱሪዝም ቦርድን አልተቋቋመም፣

የሚሉ ናቸው።

111. በመሆኑም በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን ድክመቶች እና ችግሮች ለማስወገድ ወይንም ለማቃለል አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል አቅርበናል።

# ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሀሳብ /Recommendation/

112. የቱሪዝም መዳረሻ ልማትና አገልግሎት አሰጣጥ ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ ጋር በተያያዘ ከላይ የተጠቀሱ የአሰራር ክፍተቶችን ለማሻሻል የሚከተሉትን የማሻሻያ ሀሳቦች አቅርበናል።

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በቱሪስት መዳረሻ ቦታዎች መሟላት ያለበትን አነስተኛ መስፈርት/ ስታንደርድ ሊያዘጋጅና ከክልችና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ገር በመሆን ወደ ትግበራ ሊያስገባ ይገባል። ለብሔራዊ ፓርክነት ለመመረጥ መሟላት ያለበትን ዝቅተኛ መስፈርትና አስፈላጊ የአገልግሎት መስጫ ተቋማት በግልጽ ተለይተው ሊቀመጡና በዚህ መስፈርት መሰረት ሊቋቋሙ ይገባል።
- በአገሪቱ የተቋቁመው አገልግሎት በመስጠት ላይ ያሉ ብሔራዊ ፓርኮች ውስጥ የፓርክ አስተዳደር ዕቅድ (Park Management Plan) የተዘጋጀላቸው በዕቅዱ መሰረት ወደ ተግባር ሊገቡ እና ሚኒስቴር መ/ቤቱም ተግባራዊነታቸውን ሊቆጣጠር ይገባል። የፓርክ አስተዳደር ዕቅድ (Park Management Plan) ያልተዘጋጀላቸው ብሔራዊ ፓርኮችም ዕቅዱን በማዘጋጀት ወደተግባር ሊገቡ የሚገባና ሚኒስትር መ/ቤቱም ይህ በዕቅድ ተይዞ መተግበሩን በባለቤትነት ሥራውን የሚመራውን ተቋም ሊከታተል ይገባል።
- በብሔራዊ ፓርኮች ሆነ በሌሎች የቱሪስት መዳረሻ ሥፍራዎች መሟላት የሚገባቸው መሰረተ ልማቶች እንደ ውስጥ ለውስጥ መንገድ፣ የተለያዩ አገልግሎት መስጫ (መብራት፣ ውሃ፣ የቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎቶች ሎጅ፣ ምግብ ቤቶች፣ ሱቆች፣ ህክምና መስጫዎች፣ የመጸዳጃ ቤቶች፣ የሻወር ቤቶች የመሳሰሉት) ተቋማትና አቅርቦቶች ሊሟሉላቸውና ያልተሟሉትንም በጥናት በመለየት የየሚሟሉበት ሁኔታ ሊያመቻች ይገባል። በተለይ በብሔራዊ ፓርኮች ውስጥ ቱሪስቶች መስህቦቹን በመዘዋወር በቀላሉ መጎብኘት እንዲችሉ የውስጥ ለውስጥ መንገዶች ደረጃቸውን የጠበቁ ሊሆኑ እና በየጊዜው እንክብካቤና ጥገና ሊከናውንላቸው የሚገባና ይህ መተግበሩንም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሊያረጋገጥ ይገባል።
- ለቱሪዝም ዘርፍ ልማት ኢንቨስትመንት ላይ አላሡራ ያሉ የአሰራር ማዕቀፎችና ትግበራዎች በጥናት የተለዩት ወደ ትግበራ እንዲገቡ ያልተጠኑት ደግሞ ከሚመለከታቸው የፌዴራል፣ የክልል እንዲሁም የግሉ ዘርፍ ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ እንዲጠኑና ተለይተው እንዲሻሻሉ በማድረግ ዘርፉ እንደ ሀገር ሊያበረክት የሚችለውን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም እንዲያስገኝ እና በአገሪቱ የ10 ዓመት መሪ ዕቅድ በዘርፉ ለማሳካት የታሰበውን ዕውን እንዲሆን ሊያደርግ ይገባል።


- የቱሪስት መዳረሻ ቦታዎች በሚኒስቴር መ/ቤቱ፣ ለእርሱ ተጠሪ በሆኑ ተቋማት እና በሌሎች አካላት እየተከናወኑ ያሉ ፕሮጀክቶች እና የመሰረተ ልማት ሥራዎች በተያዘላቸው በጀት እና ጊዜ ደረጃቸውን ጠብቀው እየተከናወኑ መሆናቸውን ሚኒስቴር መ/ቤቱ የቅርብ ክትትል ሊያደርግና በየጊዜው በመገምገም ግበረ መልስ በመስጠትና ተጠያቂነትን ጭምር በማስፈን እንዲጠናቀቁ በማድረግ ጎብኙዎች ደረጃውን የጠበቀ አገልግሎት እንዲያገኙ ሊያድግና መስህቦቹ ለሚገኙባቸው ህብረተሰብ ክፍሎች የሥራ ዕድል የሚፈጠርበትን ሁኔታ ሊያመቻች ይገባል።
- በቱሪስት መዳረሻ ሥፍራዎች ውስጥ መጀመሪያ ደረጃ ህክምና የሚሰጥበትን ሁኔታ እንዲሁም በአቅራቢያው ከሚገኙ ተቋማት ጋር በመቀናጀት ለሚከሰቱ ድንገተኛ የጤና ዕክሎች ጎብኚዎች ህክምና የሚያገኙበትን ሁኔታ ሚኒስቴር መ/ቤቱ፣ በሥሩ ካሉ ተጠሪ ተቋማት፣ ከሚመለከታቸው የፌዴራል፣ የክልል እንዲሁም ከግሉ ዘርፍ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ጋር በመሆን ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅበታል።
- ሚኒስቴር/መቤቱ የቱሪስት አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች ከሆቴሎች በስተቀር ለሌሎቹ (ሬስቶራንት፣ ሎጅ፣ ፔንሲዮን፣ የባህል ምግብ ቤቶች፣ አስጎብኝ ድርጅቶች) በየደረጃቸው ማሟላት የሚገባቸውን ዝርዝር መስፈርት ለያወጣላቸውና በኢትዮጵያ ደረጃዎች አገልግሎት በማቅረብ ደረጃዎቹን ሊያጸድቅና ወደ ትግበራ ሊገባ ይገባል። (ሆቴል) በየጊዜው እየመዘነ ደረጃ ሊሰጥ ይገባል።
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሆቴሎች የደረጃ ምደባ አገልግሎት በአደረጃጀት የታገዘ እና በዕቅድ ላይ የተመሰረተ እንዲሆን በማድረግ በዘመቻ መልክ የሚከናወነውን የምደባ ሥራ ማስቀርት ይጠበቅበታል። ተገንብተው ወደ አገልገግሎት የገቡ አዳዲስ ሆቴሎችን በተቀመጠው መመሪያ መሰረት በደረጃ የመመደብ ተግባር ሊከናወን በተለይም ከቀረጥ ነጻ እቃዎችን አስገብተው አገልግሎት መስጠት የጀመሩ አዳዲስ ሆቴሎች አገልግሎት በተቀመጠው አሰራር መሰረት ሥራ ከጀመሩ በአንድ አመት ጊዜያት ውስጥ ሊመዘኑና ደረጃ ሊሰጣቸው ይገባል።
- በሆቴሎች ደረጃ ምደባ መመሪያ ቁ.1/2014 መሰረት አስገዳጅ ተብለው የተቀመጡት መስፈርቶች በተለይ የእሳት አደጋ መከላከያ መስፈርቶች ሳይሟሉ ደረጃ መስጠት መቆም አለበት። በበተጨማሪም የደረጃ ምደባ ከተከናወነ በኃላ ውጤቱ በተቻለ ፍጥነት የምደባው ውጤት ለተመዘነው ድርጅትም ሆነ ለህዝቡ ይፋ ሊደረጉ እና ውጤቱን ለማሳወቅ እስከ ሁለት አመት ድረስ የሚቆየው መዘግየትን ሊያስቀርና በተለያየ ምክንያት የሚያዘገይቱም ላይ የተጠ□ቂነት አሠራር ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል።

- በደረጃ የሚመዘኑ ሆቴሎችን የዕሳት አደጋ አስገዳጅ መስፈርት ስለማሟላታቸው ለመመዘን የሚያስችል ስታንዳርድ ከኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ፣ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የእሳትና አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን እና ከሚመለከተው የዘርፉ አካላት ጋር በመተባበር እንዲዘጋጅ ሊያደርግ ይገባል።
- የኮከብ ደረጃ የተሰጣቸው ሆቴሎች በዕቅድ ላይ የተመሰረተ በዓመት ሁለት ጊዜ የክትትል ሊደረግላቸው የሚገባና በተቀመጠው መስፈርት መሰረት በመሉ ሊገመገሙ፣ የክትትል ባለሙያዎቹም የክትትትሉ ውጤትን መሰረት በማድረግ የውሳኔ ሃሳብ ሊያቀርቡ እና በሚመለከተው አካል ጸድቆ ውሳኔ ሊሰጥና በውሳኔው መሰረት የማስተካከያ እርምጃ ሊወሰድ የሚገባና ይህን በማያሟሉ አካላት ላይም ተጠያቂ የሚደረጉበት አሠራር ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል። ከክትትል በተጨማሪ ሁሉም የኮከብ ደረጃ የተሰጣቸው ሆቴሎች ደረጃው ከተሰጣቸው ከሦስት ዓመታት በኋላ የዳግም ደረጃ ምደባ ስራ ሊከናወንላቸው እና ይህም በዕቅድ ሊደገፍ ይገባል።
- በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተጀመረው የቱሪዝም መዳረሻ አስተዳደር መረጃ ስርዓት /Tourism Destination Management Information System/ በፍጥነት ተጠናቆ ወደ ተግባር ሊገባ እና ጎብኚዎችም ሆኑ ሌሎች አካላት በቀላሉ መረጃ የሚያገኙበትና የሚለዋወጡበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል። በተጨማሪም ቱሪስቶች በመዳረሻ ስፍራዎች ላይ ያለቸውን አስተያየትና ግበረ መልስ የሚሰጡበት አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል።
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ቱሪዝም ልማት ዘርፍ የሚመለከታቸውን  የግል፣ የፌዴራል እና የክልል መንግስት ተቋማትን በማስተባበር የኢትዮጵያ ቱሪዝም ቦርድ እንዲቋቋም ሊያደርግ ይገባል። በተጨማሪም ከሚመለከታቸው የፌዴርልና የክልል ባለድርሻዎች፣ ከግል ባለሀብቱ እና ከአለም አቀፍ ተቋማት ጋር በትብብር የሚሰራበትን የአሰራር ማእቀፍ ሊዘረጋ፣ ዘርፉን ለማገዝ የተፈቀዱ የቀረጥ ነጻ መብቶች ለተባለላቸው ዓላማ መዋላቸውን ሊያረጋግጥና እንዲሁም ቱሪስቶች በሚሄዱባቸው ሥፍራዎች ሁሉ ተገቢውን አገልግሎት የሚያገኙበትንና የቱሪስት ፍሰቱ የሚጨምርበትን ሁኔታ በማመቻቸት በቱሪዝም ዘርፍ ለማሳካት የታቀደውን ከግብ ሊያደርስ ይገባል።

በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት የቱሪዝም ሚኒስቴር የበላይ ሥራ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች እንዲሁም መረጃ የሰበሰብንባቸው የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት የስራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ለኦዲቱ ሥራ መሳካት ላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን።

# አባሪ 1 የሚኒስቴሩ ድርጅታዊ መዋቅር

## የቱሪዝም ሚኒስቴር ድርጅታዊ መዋቅር



# አባሪ 2፡ ኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች

| የኦዲት መመዘኛ መስፈርት/Audit Evaluative Criteria |
|---|
| 1. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በቱሪስት መዳረሻ ስፍራዎች ላይ ለሚካሄዱ የመሰረተ ልማት ግንባታዎች የህግ ማዕቀፎን ሊያዘጋጅ፣ አፈጻጸማቸውን ሊከታተል ይገባል። <br>*ምንጭ፡- የቱሪስት ፋሲሊቲና ግንባታ መሰረተ ልማት ማስፋፊያ የስራ ዝርዝር መግለጫ፣ ገጽ 4* |
| 2. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የቱሪዝም ኢንቨስትመንትን ለማሳደግ ማነቆ የሆኑ የህግ ማዕቀፎችን በመለየት እንዲሻሻሉ ሊያደርግ፣ አዳዲስ ማዕቀፎችን ሊያዘጋጅ፣ በስራ ላይ እንዲውሉ ሊያደርግ እንዲሁም አፈጻጸማቸውን ሊከታተል ይገባል። <br>*ምንጭ፡- የቱሪስት መስህብና ምርት ክፍል የስራ ዝርዝር መግለጫ፣ ገጽ4* |
| 3. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የቱሪስት መስህብ ልማትን የተመለከቱ ስታንዳርዶች እንዲዘጋጁ፣ በስራ ላይ እንዲውሉ ሊያደርግና ለአፈጻጸማቸው ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል ። *ምንጭ፡- የቱሪስት መስህብና ምርት ክፍል የስራ ዝርዝር መግለጫ፣ ገጽ 4* |
| 4. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ብሄራዊ ፓርኮች ሊያሟሉ የሚገባውን መሰረተ ልማትና አገልግሎት የሚገልጽ ስታንዳርድ በማዘጋጀት በስራ ላይ እንዲውል ሊያደርግና አፈጻጸሙን ሊከታተል ይገባል። <br>*ምንጭ፡- የቱሪስት መስህብና ምርት ክፍል የስራ ዝርዝር መግለጫ፣ ገጽ 4* |
| 5. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በነባር የቱሪዝም መዳረሻዎች የሚስተዋሉ የመሰረተ ልማት ክፍተቶችን በሚመለከታቸው አካላት በጥናት መለየታቸውንና መቀረፋቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል። *ምንጭ፡- የአስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣ አዋጅ ቁ.1263/2021* |
| 6. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በነባር የቱሪዝም መዳረሻ ስፍራዎች ላይ እየተካሄዱ ያሉ የመሰረተ ልማት ግንባታ ፕሮጀክቶች ወደ ትግበራ ከገቡ በኋላ በተያዘላቸው የጊዜ ገደብና ጥራት ደረጃ መጠናቀቃቸውን ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል። <br>*ምንጭ፡- የቱሪስት መስህብና ምርት ክፍል የስራ ዝርዝር መግለጫ፣ ገጽ 3* |
| 7. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለብሄራዊ ፓርኮችና ቅርሶች አስተዳደር የተዘጋጀው እቅድ/ManagementPlan ላይ የተጠቀሱ የመሰረተ ልማት ግንባታዎች በታቀደው መሰረት እየተፈጸሙ ስለመሆ ክትትልና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል። *ምንጭ፡- የብሄራዊ ፓርኮች ማኔጅመንት ፕላን፣ ገጽ 7* |
| 8. የቱሪዝም ሚኒስቴር በቱሪስት መዳረሻ አካባቢዎች የቱሪስቶችን ጤንነት ለማስጠበቅ የሚያስችሉ የጤና አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች መኖራቸውንና ተገቢውን አገልግሎት እየሰጡ መሆኑን ለመከታተልና ለመቆጣጠር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል። <br>*ምንጭ፡-የቱሪዝም የአስር አመት የልማት እቅድ፣ ገጽ 71* |
| 9. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ብሄራዊ ፓርኮች በሚገኙባቸው የቱሪስት መዳረሻ አካባቢዎች ለቱሪስት በሚመች መልኩ የውስጥ ለውስጥ የተሸከርካሪ እና የእግረኛ መንገድ በመዘርጋት ለቱሪስቶች ምቹ መደረጋቸውን የሚያረጋግጥበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል። <br>*ምንጭ፡-የቱሪዝም የአስር አመት የልማት እቅድ፣ ገጽ 71* |
| 10.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የቱሪስት መዳረሻ (ሆቴሎች፣ ሎጆች.....) ልማት ክፍተት የሚስተዋልባቸውን ስፍራዎች በጥናት በመለየት የግል ባለሃቶችን በዘርፉ እንዲሳተፉ የሚያሰችል ስርአት ሊዘረጋና አፈጻጸሙን ሊከታተልና ሊቶጣጠር ይገባል። <br>*ምንጭ፡- የቱሪዝም የአስር አመት የልማት እቅድ፣ ገጽ 69* |
| 11.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የቱሪስት አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶችን (ሆቴል፣ ሎጅ፣ የባህል ቤቶች) በየጊዜው እየመዘነ ደረጃ ሊሰጥ ይገባል። <br>*ምንጭ፡- የቱሪስት አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች የኮከብ ደርጃ ምደባ መመሪያ ቁ.1 /2014፣ ገጽ 19* |
| 12.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሆቴሎች ደረጃ ምደባ አሰጣጥ ትክክለኛውን መስፈርት ተከትሎ የተከናወነ ስለመሆኑ ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል። <br>*ምንጭ፡- የቱሪስት አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች የኮከብ ደርጃ ምደባ መመሪያ ቁ.1 /2014 ገጽ 19* |
| 13.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የቱሪስት አገልግት ለመስጠት ለተቋቋመ ድርጅት አገልግሎት መስጠት ከጀመረበት በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ የኮከብ ደረጃ ምደባ ሊያካሂድ እና ከ3 አመታት በኋላ የዳግም |

| የኦዲት መመዘኛ መስፈርት/Audit Evaluative Criteria |
|---|
| ደረጃ ምደባ ሊያካሂድ ይገባል።<br>***ምንጭ፡- የቱሪስት አገልጎሎቶች ብቃት ማረጋገጥና ደረጃ ምደባ ዋና ስራ አስፈጻሚ የሥራ ዝርዝር መግለጫ፣ በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን የተዘጋጀ፣ ገጽ 4*** |
| 14.ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለአገር ውስጥና ለውጭ ባለሀብቶች የተሟላ የቱሪዝም መረጃ ለመስጠት የሚያስችል ዘመናዊ የመረጃ ስርዓት ዘርግቶ ተግባራ ሊያደርግ ይገባል።<br>***ምንጭ፡- የቱሪስት መስህብና ምርት ክፍል የስራ ዝርዝር መግለጫ፣ ገጽ 4*** |
| 15.ሚኒስቴር መ/ቤቱ በቱሪስት መስህብና መዳረሻ ስፍራዎች የሚያስፈልጉ የቱሪት ፋሲሊቲ እንዲደራጁ ሊያደርግ ይገባል።<br>***ምንጭ፡- የቱሪስትፋሲሊቲ ግንባታና መሰረተ ልማት ማስፋፊያ እና የቱሪዝም መስህብና ምርት ክፍል የስራ ዝርዝር ገጽ 6*** |
| 16.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የኮከብ ደረጃ በተሰጣቸው ሆቴሎች ላይ የቱሪስቶችን የእርካታ ደረጃ ለመመዘን እንዲቻል ወቅታዊ መረጃ የሚሰበሰብበትና የሚጠናቀርበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል።<br>***ምንጭ፡-የቱሪስት አገልጎሎቶች ብቃት ማረጋገጥና ደረጃ ምደባ ዋና ስራ አስፈጻሚ የሥራ ዝርዝር መግለጫ፣ ገጽ 6*** |
| 17.ሚኒስቴሩ ዘመናዊ የቱሪዝም መዳረሻ ስርዓትን (Tourism Destination Management System) ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል።<br>***ምንጭ፡- የቱሪስት ፋሲሊቲና ግንባታ መሰረተ ልማት ማስፋፊያ የስራ ዝርዝር መግለጫ፣ ገጽ 5*** |
| 18.ሚኒስቴር መ/ቤቱ በቱሪስት መዳረሻ ቦታዎች የመሰረተ ልማት ውስንነቶች በቅንጅት እንዲቀረፉ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ስትራቴጂካዊ ግንኙነት መስርቶ ሊሰራ ይገባል።<br>***ምንጭ፡-የቱሪስት ፋሲሊቲ ግንባታና መሰረተ ልማት ማስፋፊያ ዋና ስራ አስፈጻሚ፣ የስራ ዝርዝር መግለጫ፣ በሲቪል ሰርቪስ የተዘጋጀ፤ ገጽ 4*** |
| 19.ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክልል የቱሪዝም አካላት ጋር በጋራ የሚሰራበትን ማዕቀፍ በማዘጋጀት በሥራ ላይ ሊያውል ይገባል።<br>***ምንጭ፡- ምንጭ፡ የአስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣ አዋጅ ቁ.1263/2021*** |
| 20. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የቱሪዝም ልማት ዘርፍ የሚመለከታቸውን የግል፣ የፌዴራል እና የክልል መንግስት ተቋማትን ለማስተባበር የኢትዮጵያ ቱሪዝም ቦርድ በሕግ እንዲደራጅ ሊያደርግ ይገባል።<br>***ምንጭ፡- የቱሪዝም ሚኒስቴር ማቋቋሚያ አዋጅ ቁ. 1263/2014*** |
| 21.ሚኒስቴር መ/ቤቱ በቱሪስት አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች በኩል የሚቀርቡ ቅሬታዎችን ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ኮሚቴ አዋቅሮ ሊሰራ ይገባል።<br>***ምንጭ፡ የቱሪስት አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች ደረጃ ምደባ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 173/2001፣ ገጽ 5204*** |

## አባሪ ሦስት፡ በኦዲት ቡድኑ በዕቅድ ተይዘው የታዩ የመስክ ስፍራዎች/ መ/ቤቶች

1. በማዕከላዊ ኢትዮጵያ የሶዶ ወረዳ ባሕልና ቱሪዝም ጽ/ቤት፣
2. ሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ባሕልና ቱሪዝም ቢሮ፣
3. ስንቅሌ የቆርኬዎች መጠለያ ብሔራዊ ፓርክ፣
4. አብጃታ ሻላ ሐይቆች ብሔራዊ ፓርክ፣
5. ኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ባሕልና ቱሪዝም ቢሮ፣
6. አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባሕል፣ ኪነጥበባትና ቱሪዝም ቢሮ፣
7. የኢትዮጵያ ዱር እንስሳ ጥበቃ ባለስልጣን፣
8. የኢትዮጵያ ቅርስ ጥበቃ ባለስልጣን፣

**ቃለ-መጠይቅ ተልኮላቸው የመለሱ ብሔራዊ ፓርክ ጽ/ቤቶች**

1. አዋሽ ብሔራዊ ፓርክ ጽ/ቤት፣
2. ገራኢሌ ብሔራዊ ፓርክ ጽ/ቤት፣
3. ባቢሌ የዝሆኖች መጠለያ ብሔራዊ ፓርክ ጽ/ቤት፣
4. ጋምቤላ ብሔራዊ ፓርክ ጽ/ቤት።